# የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ ሉቃስ እንደ ጻፈው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

# Part One

የማያሚ ክርስቲያኖች ህብረት ቤተክርስቲያን

# ማውጫ


**ክፍል ፩፡ የኢየሱስ መወለድና ልጅነቱ** 1

ጥናት 1: እግዚአብሔርን መታመን 1

ጥናት 2: የታላቁ ተስፋ ፍፃሜ 2

ጥናት 3፡ ቅድስት ማርያምና ካህኑ ዘካርያስ 3

ጥናት 4: የኢየሱስ መወለድ 4

ጥናት 5: ኢየሱስ በቤተ መቅደስ 5

**ክፍል ፪፡ የኢየሱስ ለአገልግሎት ዝግጅት** 6

ጥናት 6: በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ 6

ጥናት 7: የኢየሱስ ጥምቀት 7

ጥናት 8: ኢየሱስ በምድረ በዳ 8

**ክፍል ፫፡ የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ** 9

ጥናት 9: ኢየሱስ በምኩራብ 9

ጥናት 10: ነብይ በሀገሩ 10

ጥናት 11: ኢየሱስ በርኩስ መንፈስና በበሽታ ላይ 11

ጥናት 12: የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት 12

ጥናት 13: ኢየሱስ በሽተኞችን ፈወሰ 13

ጥናት 14: አዲስ ወይን፣ አዲስ አቁማዳ 14

ጥናት 15: ሰንበት 15

ጥናት 16: ተራ ሰዎች፣ መለኮታዊ ጥሪ 16

ጥናት 17: የተራራው ስብከት - ክፍል ፩ 17

ጥናት 18: የተራራው ስብከት - ክፍል ፪ 18

ጥናት 19: ጌታ የተደነቀበት እምነት 19

ጥናት 20: እምነት ሲፈተን 20

ጥናት 21: የኃጢአት ስርዐየትና የንስሃ ደስታ 21

ጥናት 22: የዘሪው ምሳሌ 22

ጥናት 23: ኢየሱስን ብዙ ተአምራትን አደረገ 23

ጥናት 24: አምስት እንጀራና ሁለት ዓሳ 24

ጥናት 25: እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? 25

ጥናት 26: የመገለጥ ተራራ 26

ጥናት 27: ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? 27

# መግቢያ

“የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ።” ሉቃ፡ 1 ፥ 1- 4

የሉቃስ ወንጌል ፀሀፊ ሉቃስ በትውልዱ የአሕዛብ ወገን፣ በሙያው ሃኪም (ባለመድሐኒት) ነበር(ቆላ 4:14)። ሉቃስ ከ12ቱ ሐዋሪያት ውስጥ አንዱ ባይሆንም ከሐዋሪያው ጳውሎስ ጋር በቅርብ በታማኝነት ካገለገሉት ቅዱሳን አንዱ ነበረ(2ጢሞ 4:11, ፊሊ1:24, ሐዋ 16፡10 - 11)። ሉቃስ ወንጌል የተፃፈው 59AD - 70AD አካባቢ ሲሆን፣ ጸሐፊው ሉቃስ ከዚህ በተጨማሪ የሐዋሪያትን ስራ እንደፃፈ ይታመናል።

ሉቃስ መጽሐፉን የፃፈው በዋናነት ለአሕዛብ ክርስቲያኖች ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች በሙሉ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማስረገጥ የተጻፈ መጽሀፍ ነው። የኢየሱስ የዘር ሀረግ ሲጀምር እንደ ማቴዎስ ወንጌል ከአብርሃም ዘር ሳይሆን የዘር ሀረጉ ከአዳም ወይም ከሰው ልጆች መጀመሪያ ጀምሮ እንደመጣ የሚገልጸው ለዚሁ ነው።

የሉቃስ ወንጌል በብዙ መልካም መልዕክቶች የተሞላ ሲሆን የመልዕክቱ መሃከለኛ ሐሳብ “የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና” (ሉቃ 19:10) የሚል ነው። የሉቃስ ወንጌል ከሌሎች ወንጌላት ለየት የሚያደርገው፡

- የኢየሱስን ውልደትና ዕድገት በዝርዝር የተተረከበት መጽሐፍ በመሆኑ
- አፃፃፉ ታሪካዊ ሂደትን የተከተለ መሆኑ
- በሌሎች ወንጌላት ያልተፃፉ 7 ተዐምራቶች ና 17 የክርስቶስ ምሳሌዎችን (parables) የያዘ መሆኑ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ጥናቱን ለሁላችን ይባርክልን።

# ክፍል ፩፡ የኢየሱስ መወለድና ልጅነቱ

## ጥናት 1: እግዚአብሔርን መታመን

*የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ* 1 ፡ 1 - 25

*መግቢያ፡ በዛሬው ጥናታችን ከብዙ የፀጥታ ጊዜ ወይንም የጨለማ ዘመን በኋላ የአዲስ ኪዳን ነብይ ሆኖ በጌታ ፊት መንገድ የሚጠርገውን የዩሐንስን መወለድ የምስራች መልዐኩ ሲያበስር እናያለን።*

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. ሉቃስ ይህንን ወንጌል የፃፈው ለማን ነው? የፃፈበትስ ምክንያት ምንድን ነበር? ሉቃስ መጽሐፉን ለመፃፍ የተጠቀመባቸው ምንጮችስ ምንድን ናቸው?
2. ታሪኩ በተፃፈበት ዘመን የነበረው ንጉስ ማን ይባላል? ዘካሪያስና ሚስቱ ከየትኛው ወገን ነበሩ?
3. በክፍሉ መሠረት የዘካሪያስና የኤልሳቤጥ በእግዚአብሔር ፊት የነበራቸው አካሄድ ምን ይመስል ነበር? (ቁ. 6)
4. ምንም እንኳን ያለነቀፉ በእግዚአብሔር ፊት የሚሄዱ ቢሆንም የሁልጊዜ ጥያቄያቸው ምን ነበር? ይሄ ጥያቄያቸው እግዚአብሔርን ከማገልገል አግዷቸዋልን? ለምን?
5. ዘካሪያስ በዕጣ ክፍሉ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል ሳለ መልዐክ ቆሞ ማየቱ የፈጠረበት ስሜት ምን ይመስል ነበር? ለምን?
6. በቁ. 12 ላይ "ፀሎትህ ተሰምቶልሃልና" በማለት ገና ስለሚወለደው ሕፃን ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ማንነት የዘረዘረውንና ሊደረግለት የሚገባው ጥንቃቄዎች ተወያዩበት።
7. በቁ. 15 ላይ "ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ምን ያህል በእናት ሆድ ላለው ፅንስ ትኩረት እንደሚሰጥ ተወያዩበት።
8. መልዐኩ ገብርኤል ተልኮ የመጣበትን ዓላማ ተናግሮ በጨረሰ ጊዜ የዘካሪያስ ምላሽ ምን ነበረ? ይህን ሁሉ ዓመታት ለለመነው የፀሎት ጥያቄ መልስ ሲመጣለት ያለማመኑ ምክንያት ምን ነበር?
9. ኤልሳቤጥ መፀነሷን ባወቀች ጊዜ ምን አለች? በውስጧ ምን ዓይነት ስሜት ሊፈጠር እንደሚችል ትረዳለህ?

*ማዛመድ:*

10. ዘካሪያስና ኤልሳቤጥ ለብዙ ዘመን የለመኑትን ልመና ከብዙ ዓመታት በኋላ በእርጅናቸው መመለሱን ስትመለከት እግዚአብሔር እንዴት ባለ መልኩ ፀሎትን እንደሚመልስ ትረዳለህ? እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ሰርቶና ጨርሶ የሚሰጠን የፀሎት ምላሽ ምን ያህል የተዋበና የሚሻል መሆኑን ለሌሎች አካፍል።
11. በእግዚአብሔር ቃል አለማመን ጉዳት እንደሚያመጣ ከዘካሪያስ ህይወት ተረዳህን?
12. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

*ማጠቃለያ፡*

በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ በመሆን በእግዚአብሔር ፊት በእምነት ፀሎት ልጅን ሲጠብቅ የነበረው ዘካሪያስ ፀሎቱ ተሰምቶ መልዐኩ ሲገለጥ በዚያው እምነት የአምላኩን መቻል ሳይሆን የተመለከተው የራሱንና የሚስቱን እርጅና ነበር። እግዚአብሔር የተናገረውን ተስፋ በራሱ ጊዜና ሰዓት በእርግጥ ይፈፅማል። የተናገረውን ሁሉ እስኪፈፅመው በእምነትና በፅናት ሁላችንም ልንጠብቀው ይገባናል።

*የቃል ጥናት - ሉቃ 1:25*

*ነቀፌታዬን ከሰው መካከል ያስወግድልኝ ዘንድ ጌታ በተመለከተ ወራት እንዲህ አድርጎልኛል*

# ጥናት 2: የታላቁ ተስፋ ፍፃሜ

<u>የምንባብ ክፍል ፡ </u>ሉቃ 1 ፡ 26 - 38

<u>*መግቢያ*</u>*፡ ባለፈው ጥናታችን ለካህኑ ዘካሪያስ መልአኩ መልአክ ተገልጦ የምስራችን እንዳበሰረው ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ለታጨች ለድንግል ማርያም ሲገለጥ እናያለን።*

<u>*የመወያያ ጥያቄዎች:*</u>

1. *ማርያም ትኖርበት የነበረበት ከተማ ማን ይባላል? በእስራኤልና በገሊላ (በተለይም በናዝሬት ከተማ) በሚኖሩ አይሁድ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ (ማቴ 4፡ 15 ፥ ዮሐ 1 ፡45 - 46)። ማርያም በምን ዓይነት ሁኔታ ትኖር ነበር? ቁ27*
2. *በቁ 29 ማርያም ከመልአኩ ሠላምታ የተነሳ የደነገጠችው ለምን ይመስልሃል? ከዚህ ተነስተን ስለማርያም ምን ማለት እንችላለን? በቁ 28 ላይ "ጸጋ የሞላብሽ ሆይ" ከሚለው ከመልዐኩ ቃል ጋር በማያያዝ ተወያዩበት።*
3. *ከቁ 31-35 መልዐኩ ስለሚወለደው ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን አንድ በአንድ ከኢሳ 9 6-7 እና ከኤር 33፡ 17 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት። በነብያቱ ዘመን የተነገረው ታላቁ ተስፋ እየተፈፀመ እንዳለ ከክፍሉ ታስተላለህን? ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊነትና* (diety) *ሰዋዊነት* (humanity) *መልአኩ እንዴት ባለ መልኩ እንደገለፀው ተወያዩበት።*
4. *በቁ 34 ላይ ማርያም መልአኩን "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?" ያለችው ካለማመን ወይንስ ማብራሪያን ከመፈለግ? ባለፈው ካጠናነው ከዘካርያስ ታሪክ ጋር ይህን ታሪክ አዛምድ።*
5. *በቁ.35 "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል" ይላል። በዚህ ታላቅ የተስፋ ፍፃሜ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ እንዴት እንደነበረ ትመለከታለህ? ይጸልልሻል ሲል ምን ማለቱ ነው?*
6. *በመጨረሻም ማርያም በቁ 38 ላይ ምን አለች? ይህ ምንን ያሳየናል?*

<u>*ማዛመድ*</u>:

7. *እግዚአብሔር በዘመናት መካከል የሚሰጠው ተስፋና ቃል ጊዜውን ጠብቆ እንደሚፈፀም ከዛሬው ጥናት ተማርክ?*
8. *"እነሆኝ . . . እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" ማለት ምን ያህል በረከት እንደሆነ እናስተውላለን? ተወያዩበት።*
9. *ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።*

<u>*ማጠቃለያ፡*</u>

*በዘመናት መካከል የገባውን የተስፋ ቃል በሁሉን ቻይነቱ ማንም ሳያግደው ሊፈፅም የሚቻለው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው። ቅድስት ማርያም "እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" በእምነት ማለቷ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሐሳብና አጀንዳ ውስጥ እንድትቀላቀል አድርጓታል። እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሰራና የገባውን ተስፋ እንዲፈፅም ቃሉን በእምነት ልንቀበለውና ልንታዘዘው ይገባናል።*

<u>*የቃል ጥናት - ሉቃ* 1:38</u>

*እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ*

## ጥናት 3፡ ቅድስት ማርያምና ካህኑ ዘካርያስ

<u>የምንባብ ክፍል ፡ </u>ሉቃ 1 ፡ 39 - 80

<u>መግቢያ</u>፡ ባለፈው ጥናታችን መልአኩ ለማርያም እንደተገለጠና ታላቅ ዜናን እንዳበሰራት ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ማርያም፥ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ከመልአኩ የሰሙትን ዜና እንዴት አድርገው እንደተቀበሉትና ምን ዓይነት እርምጃን እንደወሰዱ እንመለከታለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. ማርያም መልአኩ ከእርስዋ ከሄደ በኋላ የወሰደችው እርምጃ ምንድ ነው? ለምን?
2. ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ምን ተፈጠረ?
3. በቅድስት ማርያም ዙርያ ጥራዝ ነጠቅ ይሆኑ አስተሳሰቦች በተለያዩ ሰዎች ዘንድ ይንፀባረቃሉ። በቁ. 28 (ፀጋ የሞላብሽ)፥ ቁ.42 (ከሴቶች መካከል)፥ ቁ.43 (ብፅዕት) እና ቁ.48 (የጌታዬ እናት) መሠረት ስለቅድስት ማርያም ተወያዩ።
4. ማሪያም ቁ.47 "መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች/ my spirit rejoices in God my Savior" ባለችው ሐሳብ ላይ ተወያዩ። ከቁ 46-55 ላይ ማርያም ከፀለየዘው ፀሎት በመነሳት ስለ ህይወቷ ምን ማለት እንችላለን?
5. ካህኑ ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ "ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና" ሲል የተናገረው ስለማን ነው? "ቤዛ" ማለት ምን ማለት ነው? ዘካርያስ እያስተላለፈ ያለው መልዕክት ምንድ ነው?
6. ከቁ 69-75 የዘካርያስ መልዕክት ምንድ ነው? በቁ.70 መሠረት ቀንድ የምን ምልክት ነው?
7. በቁ. 76 ላይ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተነገረው የትንቢት ቃል ምን ነበረ? አሰተዳደጉስ ምን ይመስል ነበር?
8. በቁ.74 እና 79 መሠረት የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት የሚያመጣው ለውጥ ምንድ ነው?

<u>ማዛመድ</u>:

9. ከክፍሉ የትንቢቶችና የመልዕክቶች ዋና ሐሳብ ክርስቶስ እንደሆና ሁሉም ወደ እርሱ እንደሚያመለክቱ ትመለከታለህን?
10. የክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ምድር መምጣት ምን ያህል የታሪካችንን፥ የህይወታችንን እንዲሁም የምድራችንን ታሪክና ገፅታ እንደለወጠ ታስባለህ?

<u>ማጠቃለያ፡</u>

የክርስቶስ ኢየሱስ በስጋ ተወልዶ ወደ ምድር መምጣት ለዘመናት ሲጠበቅ የነበረው የታላቁ ተስፋ ፍፃሜ ከመሆኑ ባሻገር የቡዙዎችን ሕይወትና ታሪክ የለወጠ ታላቅ ክስተት ነው። በብሉይ ኪዳን ያሉ ነብያት ካህኑ ዘካሪያስንንና መጥምቁ ዮሐንስን ጨምሮ ስለ ኢየሱስ መምጣት ተናግረዋል አመላክተዋል። በዛሬው ጥናታችን እንዳየነው ክርስቶስ ኢየሱስ የመጣው በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ነው።

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 1:76</u>

በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን።

# ጥናት 4: የኢየሱስ መወለድ

<u>የምንባብ ክፍል :</u> ሉቃ 2 ፤ 1 - 20

*<u>መግቢያ</u>:* ባለፈው ጥናታችን ማርያም፥ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ከመልአኩ የሰሙትን ዜና እንዴት አድርገው እንደተቀበሉትና ምን ዓይነት እርምጃን እንደወሰዱ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ስለ ጌታ ኢየሱስ መወለድ እንመለከታለን።

*<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>*

1. በዘመኑ ኃያል የነበርችው የሮም ንጉስ ማን ይባላል? ከታሪኩ እንደምናየው ንጉሱ ያስተላለፈው ትዕዛዝ ምን ነበር? ማርያምና ዮሴፍስ የት ነበሩ? ወዴትስ ሄዱ? ለምን?
2. የኢየሱስን መወለድ በታላቅ ዝማሬና ደስታ መጀመሪያ ያበሰሩት እነማን ነበሩ? የተበሰረውስ ለማን ነበር?
3. እረኞች በዘመኑ ድሆች፣ አናሳ የህብረተሰብ ክፍል (low class) እንዲሁም በአይሁድ ሃይማኖት አባቶች የተገለሉ ፥ ለፍርድ ቤት ምስክርነት እንኳን የማይበቁ ነበሩ። በቁ. 8-14 መሰረት የኢየሱስን መወለድ የምስራች የመጀመሪያ ተበሳሪዎች አድርጎ እግዚአብሔር እነርሱን መምረጡ ለምን ይመስልሃል? ከ1ቆሮ 1:26-29 ጋር በማዛመድ አብራራ።
4. ኢየሱስ በከብቶች ግርግም ቢወለድም ልደቱ በብዙ የመላዕክት ዝማሬ የታጀበ ነበር። እነዚህን ሁኔታዎች አነጻጽር።
5. በቁ. 10 መልአኩ "ለህዝብ ሁሉ የሚሆን የምስራች" ሲያበስር የተወለደውን ኢየሱስ ለመግለጽ የተጠቀመበት ሶስት ቃላቶች ምንድን ናቸው? ይህን ኢሳ:-9:6 ካለው ጋር በማነጻጸር ተወያዩበት።
6. በቁ. 13 - 14 የመላዕክቶች አጀብና ዝማሬ በቁጥር እየጨመረ ሲመጣ መልአክቱ የክርስቶስን የመምጣት ዓላማ ሲናገሩ "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ" አሉ። የመልዕክቱን ትርጉም አብራራ።
7. እረኞቹ የምስራቹ ከተነገራቸውና መላዕክትም ከተለዩዋቸው በኋላ በቁ. 15-20 መሰረት ምን አደረጉ?
8. በቁ.19 ላይ "ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር" ይላል። ከዚህ ምን ትማራለህ?

*<u>ማዛመድ</u>:*

9. እረኞቹ ከመልአክቱ የሰሙትንና ያዩትን በማድነቅ ኢየሱስን ለማየት ስራቸን ሳይቀር ጥለው በአጣኝ ቄዴ ቤትልሔም መሄዳቸውን እንዲሁም ሲመለሱ እንደ ተባለላቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ መመለሳቸውን ስታይ ከእነርሱ ምን ትማራለህ?
10. መድሐኒት፣ ክርስቶስና ጌታ የሆነ ኢየሱስ በመለዱና ለእኛ የመዳን ምክንያት መሆኑ በማወቅ ምን ያህል ሀሴት በማድረግ እግዚአብሔርን ታመሰግናለህ?

*<u>ማጠቃለያ:</u>*

እግዚአብሔር በትንቢት መጽሐፍቶች ሊመጣ ስላለው መሲህ የተናገረው በዚህ ክፍል ተወልዷልና ትንቢቱ ሲፈጸም እናያለን። መወለዱን ተከትሎ የሰማይ ሰራዊትና መልአኩ በብዙ ደስታ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ለእረኞች የምስራች ሲያበስሩ፤ እንዲሁም በብዙ አድናቆት ስላዩትና ስለሰሙት ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግነዋል፤ አክብረዋል። እኛም ዛሬ ይህ የምስራች ተሰብኮልን ዳግም መወለድን አግኝተናልና ሁሌ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል።

*<u>የቃል ጥናት -</u>*

*<u>ሉቃ 2:11</u>* ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።
*<u>ሉቃ 2:14</u>* ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ

# ጥናት 5: ኢየሱስ በቤተ መቅደስ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 2 ፤ 21 - 52

*መግቢያ:* በባለፈው ጥናታችን መሲሁ እንደ ትንቢቱ ቃል በቤተልሔም ይሁዳ መወለዱን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ማርያምና ዮሴፍ ምንም እንኳን ኢየሱስ ፃድቅ ቢሆንም በግርዘት እንዲሁም በመቅደስ እንደ ህጉ ከህግ በታች ለካህኑ ሲሰጡት እንመለከታለን።

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. ከቁ.21-24 ምንም እንኳን ኢየሱስ ጌታ ቢሆንም በህግ የተሰጠውን የግርዘት ሥርዐት በስምንተኛው ቀን፤ እንዲሁም በአርባኛው ቀን ለበኩርናው የመለየትን ስርዐት (ዘፀ:- 13:11-12 ) ለእግዚአብሔር አድርጓል። ይህን በገላ:-4:1-3 ጌታችን ህግን ከመፈፀሙ ጋር ምን ዝምድና ያለው ይመስልሃል?
2. በዘሌ 12:6-8 መሠረት የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት፥ የርግብም ግልገል ወይም ዋኖስ ማቅረብ ሲገባቸው በቁ.24 መሠረት ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች ለመሥዋዕት ማቅረባቸው ስለነበሩበት የኑሮ ሁኔታ ምን ያስረዳል? ከ 2ቆሮ 8፡9 ጋር በማዛምድ ተወያዩበት።
3. ከቁ. 25-40 ህፃኑን ኢየሱስን እንደማንኛውም ህፃን ቢያቀርቡትም ስምዖን ይህ ህፃን የትንቢት ፍፃሜ ስለመሆኑ ምን ተናገረ?
4. በክፍሉ ውስጥ (በተለይም በቁ.25) የስምዖን ህይወት ምን ይመስል ነበር? ከእግዚአብሔር የተቀበለው ተስፋ ምን ነበር?
5. በቁ. 30-32 “በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን” ሲል ክርስቶስ የመጣው ለማን እንደሆነ ያመለክታል? ስምዖን ይህን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?
6. ስምዖንና ሃና እግዚአብሔርን ሲጠብቁት ስለነበራቸው ህይወትና የተስፋውን ፍፃሜ ግለፅ። ሃናና ስምዖን ኢየሱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመለከቱት የሰጡት ምላሽ ምን ነበር?
7. ከቁ 42 51 ኢየሱስ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ ይሆነውን በዝርዝር ተወያዩ።
8. በቁ.52 የኢየሱስ የእድገት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?

*ማዛመድ:*

9. እግዚአብሔር የተናገረው ቃል (ተስፋ) ይጠባበቁ ከነበሩት ከስምዖንና ከሃና ህይወት ምን ተማርክ?
10. ክርስቶስ ለሰው ሁሉ የመጣ መድኃኒትና ብርሃን እንደሆነ ተረድተህ ለሌሎች ትናገራለህን?
11. የኢየሱስ ዕድገት በሰውም በእግዚአበሔርም ፊት መልካም እንደነበረ አይተናል። አንተስ ዕድገትህ መልካም እንዲሆን የረዳህ ነገር ምንድን ነው? ለቡድኑ አካፍል።

*ማጠቃለያ፡*

*ማርያምና ዮሴፍ እግዚያብሔርን የሚፈሩ ትዕዛዙንም የሚያከብሩ ስለነበሩ በህጉም መሰረት ህፃኑን ኢየሱስ ወደ መቅደስ እንዳመጡ ተመልክተናል። በክፍሉም የእግዚአብሔርን ተስፋ ተግተው በፅናት ሲጠባበቁ የነበሩ ተስፋቸው ተፈፅሞ የዓለምን ቤዛ በአይናቸው ተመልክተዋል። በተለይም የእስራኤልን መጽናናት ሳያይ ሞትን እንዳይሞት በእምነት የተረዳው ስምዖን ተስፋው ተፈፅሞ መድሐኒዓለምን አግኝቶ ሲያቅፈው በታላቅ ደስታና እርካታ “ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ” በማለት ሲናገር ተመልክተናል። እግዚአብሔር ስለ እኛ የተናገረው ወይንም እኛ በመንፈስ የተረዳነውን ተፈፅሞ በህይወታችን ማየት ትልቅ ስኬት ነው።*

*የቃል ጥናት - ሉቃ 2:52:* ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።

# ክፍል ፪፡ የኢየሱስ ለአገልግሎት ዝግጅት

## ጥናት 6: በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ

<u>የምንባብ ክፍል ፡</u> ሉቃ 3 ፤ 1 - 22

<u>መግቢያ:</u> ባለፈው ጥናታችን ማርያምና ዮሴፍ ምንም እንኳን ኢየሱስ ፃድቅ ቢሆንም በግርዘት እንዲሁም በመቅደስ እንደ ህጉ ከህግ በታች ለካህኑ ሲሰጡት ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ልክ በኢሳያስ ዘመን ንጉስን ለመቀበል መንገድ ይጠረግና ይዘጋጅ እንደነበረ ሁሉ መጥምቁ ዮሐንስም በነብዩ እንደተነገረው የጌታን መንገድ ሲያዘጋጅ እንመለከታለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በቁ. 1 እና 2 ላይ የተዘረዘሩት መሪዎች እነማን ናቸው? ፀሃፊው እነዚህን መዘርዘር ለምን አስፈለገው? የእነዚህ መሪዎች ሹመትና የዮሐንስ ስልጣን ልዩነት ምንድን ነው?
2. ከቁ. 3-6 ባለው ክፍል ውስጥ ዮሐንስ ስለ የኃጥያትን ስርየት እየሰበከ የንስሃ ጥምቀት ለማጥመቅ ስልጣን ማን ሰጠው? ለዮሐንስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ምን ነበር? የመጣለት ይህ የትንቢት ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው? ተወያዩበት።
3. በነብዩ ኢሳያስ አስቀድሞ የተነገረው ይህ ትንቢት ዮሐንስ ከሚናገረው የንስሃ መልዕክት ጋር እንዴት ይዛመዳል?
4. ከቁ. 7-9 ዮሐንስ ህዝቡን ምን ተናገረ? መልዕክቱስ ለማን ነበር? "ለንስሃ የሚገባ ፍሬ አድርጉ" ሲል ምን ማለቱ ነው? መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ዕጣ ፈንታው ምንድን ነው? የህዝቡ ምላሽ ምን ነበር?
5. በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ከህዝቡ የሚጠበቀው ቅድሚያ ዝግጅት ምን ይመስላል? የዮሐንስ የውሃ ጥምቀት ምንን ያመለክታል? (ትርጉሙ ምንድን ነው)
6. ከቁ. 10-14 ስትመለከት የህዝቡ ልማዳዊ ህይወት (የዘውትር ኑሮ) ምን ይመስል ነበር? ዮሐንስ ስለ እውነተኛ ንስሃ (መመለስ) ምን ይላል? እውነተኛን ንስሃ እንዴት ትገልፀዋለህ? በዚህ ክፍል ውስጥ ሕዝቡ እውነተኛ ንስሃ ውምን እንደሆነ ገብቷቸዋል ለማለት ይቻላል? እንዴት? እውነተኛ ንስሃ ምን ምን ያጠቃልላል?
7. ሄሮድስ ዮሐንስን በወህኒ ያኖረው ለምን ነው? ከዚህ በመነሳት አገልግሎት ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል ተወያዩበት።

<u>ማዛመድ:</u>

8. በአሁኑ ጊዜ እንደ ዮሐንስ ወንጌልን በድፍረትና በኃይል ለሚጠፋው ትውልድ እንዳናደርስ የሚከለክለን ምንድን ነው ትላለህ? የአንተስ ህይወት በዚህ ዙሪያ ምን ይመስላል? እንደ ዮሐንስ ዝግጅትና መሰጠትን እንደሚጠይቅ አስተዋልክን?
9. እውነተኛ ንስሃ ስታስብ ከልብ (ከሃሳብ) ጅምሮ በአንደበት ተገልጦ በድርጊት የሚታይ መሆኑን ትገነዘባለህን? ጌታ በህይወትህ በኃይል እንዲሰራ ክብሩንም እንዲገልጥ ጥርጊያ መንገድ ማዘጋጅት ይኸውም በኃጢአት መፀፀትና ንስሃ ገብቶ ፊትን ሙሉ በሙሉ ወደ ጌታ መመለስ እንደሆነ አስተዋልክን?

<u>ማጠቃለያ፡</u>
ዛሬም በህይወታችን መንገድ ጥርጊያ ከሚደረግበት መንገድ አንዱና ትልቁ ንስሃ ነው። በቁ.8 ላይ "እንግዲህ ለንስሃ የሚገባን ፍሬ አድርጉ" እንደሚል ከልብ በወጣና ፍሬ ባለው ንስሃ ከጌታ ጋር ዘወትር መጓዝ ያስፈልጋል።

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 3:8</u>
እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ

# ጥናት 7: የኢየሱስ ጥምቀት

<u>የምንባብ ክፍል :</u> ሉቃ 3 ፤ 15 - 23

*<u>መግቢያ:</u> ባለፈው ጥናታችን ልክ በኢሳያስ ዘመን ንጉስን ለመቀበል መንገድ ይጠረግና ይዘጋጅ እንደነበረ ሁሉ መጥምቁ ዮሐንስም በነብዩ እንደተነገረው የጌታን መንገድ ሲያዘጋጅ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን መጥምቁ ዩሐንስ ስለ ኢየሱስ የተናገረውን ወንጌል፥ የኢየሱስ ጥምቀት እንዲሁም በጥምቀቱ ወቅት የሆኑትን ነገሮች እንመለከታለን።*

*<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>*

1. *በክፍሉ ላይ ህዝቡ መጥምቁ ዮሐንስ ማነው ብለው ያስቡ ነበር? መጥምቁ ዮሐንስስ ራሱን ማን ብሎ አስተዋወቃቸው?*
2. *መጥምቁ ዩሐንስ ለመጀመሪያ ጊዜ መልካሙን የምስራች (ወንጌል) በዚህ ክፍል ውስጥ ለህዝቡ ሲሰብክ እንመለከታለን። ምን ብሎ ሰበከላቸው? "በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል" የሚለውን ሀሳብ ተወያዩበት።*
3. *ህዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ። ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ የውሃ ጥምቀት መጠመቅ ለምን አስፈለገው? ሰማይ ተከፍቶ መንፈስ ቅዱስ በአካል መልክ እንደ እርግብ በእርሱ ላይ የወረደው ኢየሱስ ምን ሲያደርግ ሳለ ነው? መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ መውረዱ እርሱ ክርስቶስ (የተቀባ) ስለመሆኑ ማሳያ እንደሆነ ትረዳለህ? ተወያዩበት።*
4. *ከሰማይ የመጣው የእግዚአብሔር አብ ድምጽ ስለ ኢየሱስ ምን ብሎ መሰከረ? በእግዚአብሔር አብ እና ውልድ መካከል ያለውን ፍጹም ህብረት እንዴት ትረዳለህ?*
5. *በቁ. 23 ኢየሱስ በ30 ዓመቱ አገልግሎቱን እንደጀመረ ይናገራል። ከላይ በክፍሉ እንደተጠቀሰው በመንፈስ መሞላቱ ለዚህ ምን ያህል አስፈላጊ ነበር ትላለህ?*

*<u>ማዛመድ:</u>*

6. *የመንፈስ ቅዱስና የእሳት ጥምቀት በዚህ ዘመን ለእኛ ለክርስቲያኖች ምን ያህል አስፈላጊ ነው ትላለህ? የመንፈስ ቅዱስ አስፈላጊነት በህይወታችንና በአገልግሎታችን ውስጥ እንዴት እንደሆነ ተወያዩበት::*
7. *ኢየሱስ አስፈላጊ በሆኑ ወቅቶች ሁሉ አስቀድሞ ወደ አባቱ ሲጸልይ እንመለከታለን። በዚህም ጥናት ውስጥ ኢየሱስ ከመጠመቁ በፊት መጸለዩ ስለጸሎት አስፈላጊነት ምን ያህል ትረዳለህ?*
8. *እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ደስ እንደሚሰኝ ከክፍሉ ተምረናል። ዛሬስ እኛ በህይወታችን እንዴት እግዚአብሔርን ማስደሰት እንችላለን?*
9. *ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።*

*<u>ማጠቃለያ:</u>*
*መጥምቁ ዮሐንስ የንስሃን ስብከት እየሰበከ ወደእርሱ የመጡትን የውሃ ጥምቀት ሲያጠምቅ ሳለ ኢየሱስ መጥቶ ሲጠመቅ ተመልክተናል። ኢየሱስ በተጠመቀበት ጊዜ እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ሲናገር መንፈስ ቅዱስም በእርግብ መልክ ሲገለጥ ተመልክተናል። "የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፣ በአንተ ደስ ይለኛል" ያለው እግዚአብሔር ዛሬም በእኛ ህይወት የልጁን መልክ ማየትን ይፈልጋል።*

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 3:16</u>
*ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፤*

# ጥናት 8: ኢየሱስ በምድረ በዳ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 4 ፤ 1 - 13

*መግቢያ*፡ ባለፈው ጥናታችን መጥምቁ ዩሐንስ ስለ ኢየሱስ የተናገረውን ወንጌል፥ የኢየሱስን ጥምቀት እንዲሁም በጥምቀቱ ወቅት የሆኑትን ነገሮች ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ምድረ በዳ እንደሄደ እንዲሁም ለ40 ቀናትም ከጾመ በኋላ ሰይጣን እንደፈተነውና ኢየሱስ በፈተናው እንዳሸነፈ እንመለከታለን።

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. ኢየሱስ በመንፈስ ተመርቶ የሄደው ወዴት ነው? የሄደበት ዓላማ ምን ነበር?
2. ሙሴ በዘፀ 24:18 ላይ እንዲሁም ኤልያስ በ1ነገ 19:8 ላይ ያለምግብ ለ40 ቀናት በእግዚአብሔር ተራራ ላይ ላይ እንደቆዩና ለአገልግሎታቸው የሚያስፈልጋቸውን ምሪት እንደተቀበሉ እናያለን። ኢየሱስ አገልግሎት ከማገልገሉ ወይም ከመፈወሱ በፊት በምድረ በዳ ለ40 ቀናት መጾሙና በጠላት መፈተኑ ምንን ያመለክታል?
3. ኢየሱስ ከጠላት ዲያቢሎስ የመጣበትን ፈተና ሊቋቋምና ሊያሸንፍ የቻለው በምንድን ነው? በዘፍ 3 ላይ ሰይጣን በኤደን ገነት አዳምንና ሔዋንን ፈትኖ እንዳሸነፋቸው እናውቃለን። በኢየሱስ እና በአዳምና ሔዋን ፈተና መካከል የነበረውን ልዩነት አስረዳ።
4. ኢየሱስ ለ40 ቀናት ከጾመ በኋላ በቁ.2 ላይ ተራበ ይላል። ዲያቢሎስም መራቡን ተመልክቶ በጉድለቱ (Physically vulnerable በሆነበት) አጋጣሚ በመጠቀም "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ" በማለት ልጅነቱን በምግብ ሲፈታተነው ስትመለከት ስለጠላት የውጊያ ስልት ምን ትረዳለህ? ኢየሱስ ድንጋዩን ዳቦ ማድረግ እየቻለ ከራሱ የስጋ ፍላጎት (ረሃብ) ይልቅ የእግዚያብሔርን ሀሳብ ለመፈፀም ያሳየውን ጭካኔ እንዴት ታየዋለህ?
5. ዲያቢሎስ በአለም የሚገኘውን ሀብት፣ ዝና፣ ክብር፣ ስልጣን ሁሉ በቅጽበት ካሳየው በኋላ "ወድቀህ ብትሰግድልኝ ሁሉ ለአንተ ይሆናል" ባለው ጊዜ የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበር? በማያሻማ መልኩ ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ የዓለምን ጥቅም ለማግኘት ኢየሱስ በእግዚአብሔር ክብር ለአንድም ጊዜ እንደማይደራደር ያሳየውን ቁርጠኝነት ምን ያህል ትረዳለህ? ተወያዩበት::
6. ዲያቢሎስ በመዝ 91:11-12 ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ኢየሱስን ሲፈትነው እናያለን። ሰይጣን ክፍሉን በሙሉ ያልጠቀሰው ለምን ይመስልሃል? ከዚህስ ምን እንማራለን? በ2ቆሮ 11:14 ላይ "ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና" ከሚለው ሐሳብ ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
7. በቁ. 13 ላይ ዲያቢሎስ ፈተናውን ከጨረሰ በኋላ ምን ሆነ ብሎ ይናገራል?

*ማዛመድ*:

8. ጌታ ኢየሱስ ከዲያቢሎስ ለቀረበለት ፈተና ሁሉ "እንዲህ ተብሎ ተፅፏል" በማለት ፈተናውን በድል አልፎታል። ዛሬስ በዚህ ዘመን ለሚደርሱብን ፈተናዎች የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል እንደሚያስፈልገን ተወያዩበት።
9. ዲያቢሎስ ፈተናውን ከጨረሰ በኋላ ምንም እንኳን ቢሸነፍም "እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ" ይላል። ትላንት ፈተናዎቻችንን በድል ማለፋችን ዛሬን እንዳያዘናጋን ይህ ምን ያስተምረናል?

*ማጠቃለያ፡*

"እንዲህ ተብሎ ተፅፏል" በማለት ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሀሳብ ሊያሰናክለው የመጣውን ጠላት ጌታ ኢየሱስ ሲቃወመው ተመልክተናል። ዛሬ እኛም በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ በየዕለቱ በመሞላት የጠላትን ሽንገላ በፅናት ልንቃወም ይገባል።

የቃል ጥናት - ሉቃ 4:8 ለጌታ አምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ

# ክፍል ፫፡ የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ

## ጥናት 9: ኢየሱስ በምኩራብ

<u>የምንባብ ክፍል ፡ </u>ሉቃ 4 ፤ 14 - 21

<u>መግቢያ፡ </u>ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ምድረ በዳ እንደሄደ እንዲሁም ለ40 ቀናትም ከጾመ በኋላ ሰይጣን እንደፈተነውና ኢየሱስ በፈተናው እንዳሸነፈ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ኢየሲስ በገሊላ በሰንበት ቀን በምኩራብ ገብቶ ሲያስተምር ወደ ምድር የመጣበትን ዓላማ ለሕዝቡ ይፋ ሲያደርግ እንመለከታለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በክፍሉ ኢየሱስ ለማገልገል የመጣበት አካባቢና ከተማ ማን ይባላል? ይህ አካባቢ ከኢየሱስ ዕድገት ጋር ምን ግንኙነት አለው? ኢየሱስ ወደዚህ ከተማ የተመለሰው በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር?
2. ኢየሱስ አገልግሎቱን በጀመረበት ወቅት የእግዚአብሔር ሞገስ በእርሱ ላይ እንደነበረ በክፍሉ (በተለይም በቁ.14-15) ምን የተፃፈ ማስረጃ ሀሳብ አለ?
3. ኢየሱስ ተወልዶ በአደገበት ከተማ በሚያውቁት በጓደኞቹና በወዳጆቹ ፊት አገልግሎት መጀመሩ ጥቅምና ጉዳቱ ምንድን ነው?
4. በቁ. 16 "እንደ ልማዱ" የሚል ቃል ተፅፏል። የኢየሱስ ልማድ ምን ነበር? ከዚህ ስለ ኢየሱስ ህይወት ምን ትማራለህ?
5. ኢየሱስ "መንፈስ በእኔ ላይ ነው" ካለ በኋላ በኢሳ:-61:1-2 ላይ የተፃፈውን የትንቢት ቃል በመጥቀስ የአገልግሎቱ ዋና ዓላማ ምን እንደሆነ ይናገራል? በክፍሉ ድሆች፥ የታሰሩ፥ ዕውሮች፥ የተጠቁ የሚላቸው እነማንን ነው? የኢየሱስ መፍትሔ ለእነሱ ምንድን ነው?
6. በክፍሉ ላይ "የተወደደውን የጌታ ዓመት እሰብክ ዘንድ" የሚለው ሀሳብ በዘሌ:-25:1-12 ላይ ከተፃፈው የኢዮቤልዩ ዓመት (የምህረትና የመመለስ ዓመት) ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
7. በአይሁድ ልማድ በምኩራብ የነብያት መጽሐፍ ከተነበበ በኋላ የማብራሪያ ስብከት ይሰጣል። ኢየሱስ በክፍሉ የሰጠው የማብራሪያ ስብከት ምን የሚል ነበር?

<u>ማዛመድ:</u>

8. ኢየሱስ አገልግሎቱን በትውልድ ከተማውና አካባቢ መጀመሩ ከዚህ ምን ትማራለህ?
9. የኢየሱስ ወደ ምድር የመምጣቱና የማገልገሉ ዓላማ መልካም የምስራች ለመስበክ እንዲሁም መፈታትን፣ ማየትንና ነፃ መውጣትን ለመስጠት መሆኑን ተገንዝበህ ይህን መልካም የምስራች (ወንጌል) ለሌሎች ታካፍላለህን?

<u>ማጠቃለያ፡</u>

ኢየሱስ በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመልሶ የህዝብ አገልግሎቱን (Public Ministry) ሲጀምር ተመልክተናል። ኢየሱስ የገዛ ወገኖቹ ባይቀበሉትም በትንቢት ስለእርሱ የተፃፈውን በማንበብ ለድሆች፣ ለታሰሩት፣ ለዕውሮችና ለተጠቁት መፍትሔ ሊሰጥ እንደመጣ ሲናገራቸው ተመልክተናል። በብሉይ ኪዳን ዘመን በኢዮቤልዩ ዓመት የታሰሩ እንደሚፈቱ፥ የተጨቆኑ ነፃ እንደሚወጡ፥ ድሆች በዕዳ የተወሰደባቸው ማናቸውም ንብረት እንደሚመለስ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚሁ የአዲስ ኪዳን ኢዮቤልዩ ሆኗል።

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 4:19</u>

የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል

# ጥናት 10: ነብይ በሀገሩ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 4 ፤ 22 -30

መግቢያ፡ ባለፈው ጥናታችን ኢየሲስ በገሊላ በሰንበት ቀን በምኩራብ ገብቶ ሲያስተምርና ወደ ምድር የመጣበትን ዓላማ ለሕዝቡ ይፋ ሲያደርግ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ኢየሱስ በአገለገለው አገልግሎት የገዛ ወገኖቹ ቢደነቁም ሲጠራጠሩት አልፈውም ተቆጥተው ከከተማ ውጭ አውጥተው ሲጥሉት እንመለከታለን።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. በምኩራብ የኢየሱስን ንግግር የሰሙት ሰዎች የተደነቁት ከምን የተነሳ ነበር? ተደንቀው ሳይጨርሱ በልባቸው የገባው ጥርጣሬ ምን የሚል ነበር?
2. ኢየሱስ የልባቸውን ሀሳብ አውቆ በቁ. 23 ላይ በምሳሌ ምን ብሎ ተናገራቸው? ይህንን ምሳሌ በሉቃ 23:35-39 ላይ ከተፃፈው ታሪክ ጋር በማዛመድ ተወያዩበት። ኢየሱስ የተናገረው ቃል ትንቢታዊ እንደሆነ ታስባለህን?
3. ኢየሱስም በመቀጠል በቁ. 24 የተናገራቸው ምሳሌ ምን የሚል ነበር? ከዩሐ 1:11 ከተፃፈው ቃል ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
4. ኢየሱስ በቁ. 23 ላይና በቁ.24 የተናገራቸውን ምሳሌዎችን ለማብራራት ከቁ. 25-27 ላይ ስለአንዲት አህዛብ መበለትና ስለአንድ አህዛብ የሰራዊት አለቃ ይናገራል። 1ነገ:-17:8-16 እንዲሁም 2ነገ:-5:8-14 ላይ ያለውን ታሪክ አንብቡ። በዚህች መበለት ሴትና በሰራዊት አለቃ ሰውዬ ህይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ሀሳብና ፈቃድ እንዲፈፀም ምክንያቱ ምንድን ነበር?
5. ኢየሱስ በምሳሌ እና በነብዩ ኤልያስና ኤልሳዕ ዘመን የሆነውን ከተናገራቸው በኋላ በምኩራብ የተሰበሰበው ህዝብ ምላሽ ምን ነበር?

ማዛመድ:

6. ዛሬስ በህይወታችን፣ በቤተሰባችንና በትውልዳችን እግዚአብሔር እንዳይሰራ የሚከለክሉ ነገሮች ምንድን ናቸው? ተወያዩበት::
7. ኢየሱስ የገዛ ወገኖቹ አገልግሎቱን ቢጠራጠሩትና ባይቀበሉትም ኢየሱስ የአባቱን ሀሳብ ከመፈፀም ወደኋላ አላለም። ከኢየሱስ ህይወት ምን ትማራለህ?
8. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

ማጠቃለያ፡

ኢየሱስ በአስተምሮቱና ከአፉ ከሚወጣው የፀጋ ቃል የተነሳ ብዙዎች እንደተነቁ ተመልክተናል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ቢደነቁም በልባቸው ስላላመኑት ሲጠራጠሩት አልፈውም ከከተማው ውጭ አውጥተው ሲጥሉት ተመልክተናል። ዛሬም የምንሰማው ቃል ካላመነውና በውስጣችን ካልተዋሃደ እግዚአብሔር በሕይወታችን ለመስራት እንደሚቸገር እንማራለን።

የቃል ጥናት - ዮሐ 1:11

የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፤ የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው

# ጥናት 11:  ኢየሱስ በርኩስ መንፈስና በበሽታ ላይ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 4 ፤ 31 - 44

መግቢያ፡ ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ በአገለገለው አገልግሎት የገዛ ወገኖቹ ቢደነቁም ሲጠራጠሩት አልፈውም ተቆጥተው ከከተማ ውጭ አውጥተው ሲጥሉት ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ኢየሱስ በቅፍርናሆም (የኢየሱስ የአገልግሎቱ መናገሻ/headquarter; ሌላ የገሊላ ከተማ) በርኩሳን መናፈስት የተያዙትን ነፃ ሲያወጣና በበሽታ የተያዙትን ሲፈውስ እንመለከታለን።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. የክርስቶስ ትምህርት ሰዎችን ያስደነቀበት ምክንያት ምን ነበር (ቁ. 31-32)?
2. ርኩሳን መናፍስቶች ኢየሱስን ሲያዩ ምን ያደርጉ ነበር?
3. በቁ.34, 41 መሰረት አጋንቶች “አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ” ሲሉ መስክረዋል። በያዕ 2:19 ላይም አጋንንቶች በእግዚአብሔር ማንነት እንደሚያምኑ እንደሚንቀጠቀጡ ይናገራል። ጌታ ኢየሱስ በዚህ ክፍል ውስጥ አጋንቶች ስለእርሱ እዳይመሰክሩ የፈለገው ለምን ይመስልሃል?
4. በክፍሉ ኢየሱስ በተደጋጋሚ በአጋንንት ተፅኖ ውስጥ የነበሩትን ነፃ ሲያወጣ እንመለከታለን። ይህ ስለእርሱ ጌትነት ምን ያስረዳሃል?
5. በክፍሉ መሰረት የጌታ ኢየሱስ መገኘት በገሊላ በተለይም በቅፍርናሆም ለተሰበሰቡት ሰዎች ምን አደረገላቸው? በበሽታና በሰይጣን አሰራር (ተፅኖ- possession and obsession) ግንኙነት ያለው ይመስልሃል? ተወያዩበት።
6. የስምዖን አማት ከብርቱ ንዳድ ከተፈወሰች በኋላ ማንን አገለገለች? ኢየሱስን ብቻ ወይስ አብረው ያሉትን ሁሉ? ተወያዩበት።
7. በቁ.43 ኢየሱስ ይፈልጉት ለነበሩት ሰዎች ምን አላቸው? ይህ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት ምን ያሳየናል?

ማዛመድ:

8. ሰዎችን ነፃ የሚያወጣ ምን ዓይነት ትምህርት እንደሆነ ታስባለህ?
9. ኢየሱስ በአጋንትና በደዌ ኃይል ላይ ያለውን ስልጣን አውቀህ የስሙን ኃይል ምን ያህል ትጠራለህ?
10. ጌታ ካለብህ ነገር ሁሉ ሲፈታህ ምን ያህል ጤናህን ሌሎችን ለማገልገል ታውላለህ?
11. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

ማጠቃለያ፡

በዛሬው ጥናታችን ኢየሱስ በአጋንትና በበሽታ ላይ ስልጣን እንዳለውና አጋንቶችም ፈፅሞ እንደሚንቀጠቀጡለት ተመልክተናል። ዛሬም የኢየሱስ ስም ኃይለኛና ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም ነው። በሰማይ በምድርም ከምድርም በታች ያሉ መናፍስቶች በኢየሱስ ስም ይንበረከካሉ።

የቃል ጥናት - ፊል 2:10

በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ

## ጥናት 12: የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ **5 ፤ 1 -11, 5 ፤ 27 - 28**

መግቢያ፡ ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ በቅፍርናሆም (የኢየሱስ የአገልግሎቱ መናገሻ/headquarter; ሌላ የገሊላ ከተማ) በርኩሳን መናፈስት የተያዙትን ነፃ ሲያወጣና በበሽታ የተያዙትን ሲፈውስ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ስምዖን፣ እንድሪያስ፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ደቀ መዛሙር እንዲሆኑ ሲጠራቸው እንመለከታለን።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. በቁ. 2 ላይ "ዓሳ አጥማጆቹ ግን ከእርሱ (ከታንኳዎቻቸው) ወጥተው መረቦቻቸውን ያጥቡ ነበር" ይላል። ይህ በወቅቱ እነስምዖን ስለነበረቡት ሁኔታ ምን ያሳያል?
2. በቁ.3 ላይ ምን ሆነ? በቁ.4 ላይ ኢየሱስ አስተምሮ ከጨረሰ በኋላ ስምዖንን ብሎ ጠየቀው?
3. ኢየሱስንና ዓሳ አጥማጆቹን በማዛመድ እንመልከት።

ኢየሱስ፡ ዓሳ የማጥመድ ልምድ አልነበረውም፤ ቃሉን ያስተምር ነበር

ዓሳ አጥማጆች: ልምድ ያላቸው ዓሳ አጥማጆች ነበሩ፤ ተስፋ ቆርጠው ነበር

በአጥማጆቹ ልምድ መሰረት መረብ ወደ ጥልቅ ተጥሎ ዓሳ የሚገኘው በሌሊት እንጂ በቀን እንዳይደለ እያወቁ ኢየሱስ ለተናገራቸው ቃል መታዘዛቸው ምን ያሳያል? ስምዖን መረቡን ወደጥልቁ ከመጣሉ በፊት ኢየሱስን ምን አለው?

5. በቁ. 5 ላይ "በቃልህ መረቦችን እንጥላለን" በማለት ለጌታ ታዘው መረባቸውን ሲጥሉ እንመለከታለን። መታዘዛቸው ምን ውጤት አመጣ? እነስምዖን በረከታቸውን ለጓደኞቻቸው ለማካፈል ምን አደረጉ?
6. በቁ.9 ላይ ጴጥሮስ ብዙ ዓሳዎችን እንደያዙ በተመለከተ ጊዜ ለኢየሱስ ምን ብሎ ተናገረ? ለምን እንደዚያ ብሎ የተናገረ ይመስልሃል?
7. በቁ.10 ላይ ኢየሱስ ስምዖንን ምን ብሎ ተናገረው? በቁ.11 ላይ "ታንኳቸውን ወደምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ትከተሉት" ይላል። ይህን ሀሳብ ከሉቃ 14:26 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
8. በቁ. 27-28 ላይ ኢየሱስ ቀራጩን ሌዊ (በኋላም ማቴዎስ የተባለው) አግኝቶ ተከተለኝ ሲለው እንመለከታለን። የሌዊ ምላሽ ምን ነበር? በደህንነቱና በመጥራቱ ደስታ ምን አደረገ?

ማዛመድ:

9. በኑሮህ ወይም በአገልግሎትህ ብዙ ደክመህ ተስፋ የቆረጥክበት ነገር ይኖር ይሁን? ከክፍሉ ምን ማድረግ እንዳለብህ ተማርክ? "አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን ጽድቅ መንግስቱንም ፈልጉ ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ 6:33 ) የሚለው ቃል ከክፍሉ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
10. "ሁሉ ትተው ተከተሉት" ከሚለው ሀሳብ ምን ተማርክ?

ማጠቃለያ፡

ስምዖንና ከእርሱ ጋር የነበሩት ለሌቱን በሙሉ ዓሳ ለማጥመድ ሞክረው ምንም ስላላጠመዱ ተስፋ በቆረጡበት ሰዓት ኢየሱስ መጥቶ ምንም እንኳን ከዕውቀታቸውና ከልምምዳቸው ውጭ በሆነ መንገድ መረቡን ወደ ጥልቁ እንዲጥሉ ሲጠይቃቸው ታዘው እንደቃሉ ሲያደርጉ ተመልክተናል። በመጨረሻም እድሜያቸውን በሙሉ የለፉበትን ኑሮአቸው የሆነውን ሥራቸውን ትተው ጌታ ኢየሱስን እንደተከተሉ ተመልክተናል።

የቃል ጥናት - ሉቃ 5:5

ሌሊቱን ሁሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ

# ጥናት 13: ኢየሱስ በሽተኞችን ፈወሰ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 5 ፤ 12 - 26

*መግቢያ*፡ ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዝሙሮችን እንደጠራ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ኢየሱስ ለምፃሙና ሽባውን ሲፈውስ እንመለከታለን።

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. በቁ.12 ለምፃሙ ሰው ወደ ኢየሱስ መጥቶ ምን አደረገ? በዘሌ 13:45-46 መሰረት በሙሴ ህግ ስለ ለምፃሞች የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው?
2. ይህ ሰው ተገልሎ ከሚኖርበት ህይወት ወደ ከተማ በመምጣት በኢየሱስ ፊት ወድቆ "ብትወድ ልታነፃኝ ትችላለህ" ማለቱ ለመዳን ስላለው ውሳኔ (ጉጉት) ምን ያሳያል? ኢየሱስ ምን አለው? ኢየሱስ ለምፃሙን ዳስሶ መፈወሱ ምንን ያሳያል? ኢየሱስ ለምፃሙን ከፈወሰ በኋላ ምን አለው?
3. በቁ. 18-19 ላይ ሽባውን ተሸክመው የመጡ ሰዎች ምን አደረጉ? ለሽባው ሰውዬ ያላቸውን ፍቅር፣ መሰጠታቸውን፣ ጥረታቸውንና እምነታቸውን ስታይ ዛሬ እንዴት ወንድም ወንድሙን ማገልገል እንዳለበት የሚያስተምር ጥሩ ምሳሌ ነው ትላለህን? ተወያዩበት:: በቁ.20 ላይ "እምነታቸውን አይቶ" ከሚለው ሃሳብ ስለ እግዚአብሔር አሰራር ምን ትማራለህ?
4. ኢየሱስ ሽባውን ፈወሶ ብቻ ወደ ቤቱ መሸኘት ሲችል ይህን ምቹ ሁኔታ ምንን ሊያስተምራቸው ተጠቀመበት? (ቁ. 24)። በክፍሉ መሠረት ኢየሱስ ማን ነው?
5. በቁ.24 ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን "የሰው ልጅ" በማለት ለህዝቡ ሲያስተዋውቅ እናያለን። በአዲስ ኪዳን ውስጥ 88 ጊዜ "የሰው ልጅ" ሲጠቀስ፣ በትንቢተ ሕዝቅኤል ብቻ 93 ጊዜ ተጠቅሷል። ኢየሱስ የሰው ልጅ ለምን ተባለ? ተወያዩበት።
6. በመጨረሻም በቁ.26 መሠረት ምን ሆነ? ይህ የእግዚአብሔር ክብርና ማዳን በሰዎች መካከል ሲገለጥ ከሚፈጥራቸው ስሜቶች አንዱ ነው ማለት እንችላለን?

*ማዛመድ:*

7. በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ለምፅ የኃጥያአት ምሳሌ ነው። ኃጥያአት እንደ ለምፅ ከእግዚአብሔርና ከህዝቡ እንደሚለይ አውቀህ ምን ያህል በንስሐ ህይወት ሁልጊዜ ሊያነፃ ወደሚችለው ኢየሱስ ትቀርባለህ?
8. በቁ.20 ላይ "እምነታቸውን አይቶ" ኢየሱስ ሽባውን እደንፈወሰ ተመልክተናል። ዛሬም እግዚአብሔር ሰው ከሚያየው የውጭ ማንነት ሳይሆን የውስጥ እምነታችንን እንደሚያከብርና እንደሚፈልግ ተረድተን ምን ያህል በፊቱ እንመላለሳለን?

*ማጠቃለያ፡*

ኢየሱስ በአስተምሮቱና ከአፉ ከሚወጣው የፀጋ ቃል የተነሳ ብዙዎች እንደተነቁ ተመልክተናል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ቢደነቁም በልባቸው ስላላመኑት ሲጠራጠሩት አልፈውም ከከተማው ውጭ አውጥተው ሲጥሉት ተመልክተናል። ዛሬም የምንሰማው ቃል ካላመነውና በውስጣችን ካልተዋሃደ እግዚአብሔር በሕይወታችን ሊሰራ ይቸገራል።

*የቃል ጥናት - ሉቃ 5:20*

እምነታቸውንም አይቶ፡- አንተ ሰው ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው።

# ጥናት 14: አዲስ ወይን፣ አዲስ አቁማዳ

<u>የምንባብ ክፍል</u> : ሉቃ 5 ፤ 29 - 39

*<u>መግቢያ:</u> ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ ለምፃሙን ሰውዬና ሽባውን እንደፈወሰ በተጨማሪም ኃጥያአትን ሊያስተሰርይ ስልጣን ያለው አምላክ መሆኑን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ኢየሱስ ስለ አዲስና አሮጌ ወይንና አቁማዳ በምሳሌ ያስተማረውን እንመለከታለን።*

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በቁ.29 መሰረት ኢየሱስ የት ነበር? ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች እነማን ነበሩ? በቁ.30-35 ላይ ኢየሱስን ምን ብለው ጠየቁት? እርሱስ ምን ብሎ መለሰላቸው?
2. "ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድሐኒት አያስፈልጋቸውም" ሲል ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለምን አይነት ሕመምተኞች ነው? ቁ.31
3. በቁ. 33 - 35 ላይ ኢየሱስን ምን ብለው ጠየቁት? ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰላቸው? ተወያዩበት።
4. የአዲስ ልብስ እራፊ ባረጀ ልብስ ላይ የማይደረገው ለምንድን ነው? ቢደረግ ምን ይሆናል? በማቴ 9:16 መሰረት ኢየሱስ ስለምን እያስተማረ እንዳለ ተወያዩበት።
5. ባረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የማይደረገው ለምንድን ነው? ቢደረግ ምን ይሆናል? ጉዳቱን ተወያዩበት። ያረጀ አቁማዳና አዲስ የወይን ጠጅ የምን ምሳሌዎች ናቸው?
6. በቁ.38 "አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል" ይላል። ስለ አዲስ ወይንና ስለ አዲስ አቁማዳ ተወያዩ። አዲስ አቁማዳ የምን ምሳሌ ነው? "ሁለቱም ይጠባበቃሉ" ሲል ምን ማለቱ ነው? ስለ መፍላተ ሂደት (Fermentation process) የምታውቁትን ተወያዩ።
7. አሮጌው ወይን ሲጠጣ አዲሱን የሚፈልግ የሌለው ለምንድን ነው? ከዚህ ምን እንማራለን? (ቁ.39)

<u>ማዛመድ:</u>

8. እግዚአብሔር አዲስ ነገርን ማድረግ የሚወድ አምላክ ነው። በራዕ 21:5 ላይ "በዙፋኑም የተቀመጠው፡- እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ" ይላል። ነገር ግን ዛሬ አዲስ ነገርን በህይወታችን እንዳንለማመድ የሚያደርገው ከክፍሉ የምንማረው ምንድን ነው? ምንስ ማድረግ አለብን?
9. አዲስ የህይወት ልምምድ ያለመለማመድ ተግዳሮት (challenge) ምንድን ነው? (ቁ.39)

<u>ማጠቃለያ፡</u>

ኢየሱስ በክፍሉ በተጠቀሰው ምሳሌ ወደ ምድር የመምጣቱን ዓላማ ሲገልፅ አሮጌውን ህይወትና ልምምድ ለመጠገንና ለማደስ ሳይሆን አዲስ ህይውትና ልምምድ ለሚያምኑት ሊሰጠን እንደሆነ ግልፅ አድርጓል። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ ከአሮጌው ህይወትና ልምምድ ወጥተን አዲሱን ለመቀበል ስንቸገር እንታያለን። ከዚህም የተነሳ ብዙዎቻችን አሮጌውን አቁማዳችንን ይዘን ተቀምጠናል። አዲስን ነገር ለመቀበል ሁሌም አዲስ አስተሳሰብ፣ ዝግጅትና ውሳኔን ይጠይቃል። እግዚአብሔር አዲሱን ወይን በህይወታችን እንዲጨምር አዲስ አቁማዳ ከእኛ ይፈልጋል። ስለዚህ ዛሬ ነገ ሳንል አሮጌውን አቁዳማችንን ልንቀይር ያስፈልግናል።

<u>የቃል ጥናት - ምሳ 16፡1</u>

የልብ መዘጋጀት ከሰው ነው፤ የምላስ መልስ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

# ጥናት 15: ሰንበት

<u>የምንባብ ክፍል</u> **፡ ሉቃ 6 ፤ 1-11**

***<u>መግቢያ፡</u>*** **ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ ስለ አዲስ ወይን ጠጅና አዲስ አቁማዳ የተናገረውን ምሳሌ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ኢየሱስ ስለ ሰንበት የተናገረውን እንመለከታለን።**

***<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>***

1. በቁ.1-5 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የት ነበሩ? "በሰንበት ሊደረግ ያልተፈቀደውን ስለ ምን ታደርጋላችሁ?" ብለው ፈሪሳዊያን ደቀ መዛሙርቱን በጠየቁ ጊዜ ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰላቸው?
2. ኢየሱስ "የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው" ብሎ ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው? ከማር 2:27 ጋር በማነፃፀር ተወያዩበት።
3. ሰንበት ማለት ምን ማለት ነው? በ ዘጸ 31፡12-17 መሠረት የሰንበት ስርዐት ለማንና ለምን ተሰጠ? ጌታ ስለ ሰንበት ያስተማራቸውን ትምህርት በብሉይ ኪዳን ከነበረው ሥርዐት ጋር በማነፃፀር ተወያዩበት?
4. የሰንበት ቀን መቼ ነበር? ዛሬስ? ለምን? የቀደሙት ሐዋሪያት ያደርጉ የነበሩትን ከሐዋ 20:7 እና 1ቆሮ 16:1-2 በማንበብ ተወያዩበት።

*/The Sabbath is a reminder of the completion of the "the old creation", while the Lord's Day is a reminder of our Lord's finished work in the "new creation". The Lord Day commemorates the resurrection of Jesus Christ from the dead as well as the coming of the Holy Spirit and the "birthday" of the Church (Act 2)/*

4. *በቁ. 6-11 የሆነው ታሪክ ምንድን ነው? "በሰንበት በጎ ማድረግ ተፈቅዶአልን ወይስ ክፉ?" ብሎ ኢየሱስ ሊያስተምራቸው የፈለገው ነገር ምንድን ነው?*
5. ዕብ *4:1-10* መሠረት ኢየሱስ የሰንበት እረፍት ነው ማለት ምን ማለት ነው? ወደ እረፍቱ የገባ (ኢየሱስ) እግዚአብሔር ከስራው እንዳረፈ እኛም ከስራ አርፈናል ሲል ምን ማለቱ ነው?

***<u>ማዛመድ:</u>***

6. ዛሬ ስለ ሰንበት ምን ተማርክ? ስለ ሰንበት ዕረፍትስ?

***<u>ማጠቃለያ፡</u>***

**የሰንበት ስርዓት ለእስራኤላዊያን የተሰጠ ትልቁ ስርዐት ነው። በሰንበት ሰው ሁሉ ከስራው ያርፋል። የሰንበት እረፍት ጥቅሙ በስራ የደከመውን ሰውነት ማሳረፍና እግዚአብሔርን ማምለክ ነው። በኢዲስ ኪዳን የቀደሙት ሕእግዚአብሔር ሁላችንም በስራ የደከመ ሰውነታችንን እንዲያርፍና እርሱን እንዲያመልከው ይፈልጋል።**

<u>**የቃል ጥናት - ሉቃ** 6:5</u>

**የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው**

# ጥናት 16: ተራ ሰዎች፣ መለኮታዊ ጥሪ

<u>የምንባብ ክፍል</u> ፡ ሉቃ **6 ፤ 12 - 16, 9 ፤ 1 - 11**

<u>መግቢያ:</u> ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ ስለ ሰንበት የተናገረውን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችንን ከደቀ መዛሙርቱ ውስጥ 12ቱን ሲመርጥና ሐዋሪያት ብሎ ሲሰይማቸው እንመለከታለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በቁ. 12 ላይ ኢየሱስ ምን አደረገ ይላል? ለምን ይመስልሃል?
2. በነጋም ጊዜ ኢየሱስ ምን አደረገ? የጠራቸውን ምን ብሎ ሰየማቸው?
3. ደቀ መዛሙርት ማለት ምን ማለት ነው? ሐዋሪያስ? ኢየሱስ ምን ያህል ደቀ መዛሙርት ነበሩት? (ሉቃ 10:1) ኢየሱስ ለምን 12 ሐዋሪያቶችን ብቻ ጠራ? (ማቴ 21:43 ፤1ጴጥ 2:9)
4. በቁ. 14-16 የሐዋሪያቱን ስም ሲዘረዝር በጴጥሮስ ጀምሮ በይሁዳ ይጨርሳል። ኢየሱስ ይሁዳን ሲመርጠው በፍፃሜው ላይ እንደሚክደው ያውቃልን? (ዮሐ 6:64) ኢየሱስ ሊሆን ያለውን እያወቀ የአባቱን ፈቃድ በምድር ለማከናውን እስከ ሞት መታመኑን እንዴት ትመለከተዋለህ?
5. ከሐዋርያቱ ውስጥ 7ቱ ዓሳ አጥማጆች (ዮሐ 21:1-3)፣ 1 ቀረጥ ሰብሳቢ (ሉቃ 5:27) ሲሆኑ የ4ቱ ስራ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በውል አልተገለጠም። ከዚህ የጌታ የኢየሱስ አጠራር ጳውሎስ 1ቆሮ 1:26-29 ላይ ከተናገረው ጋር በማነፃፀር ተወያዩበት። በእነዚህ ተራ በሚመስሉ 12 ሰዎች የምድርን ገፅታ የቀየረ ታላቅ የእግዚአብሔርን ስራ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመሰራቱ ሚስጥር ምንድን ነው ትላለህ?
6. በምዕራፍ 9:1-6 ላይ ጌታ ኢየሱስ 12ቱን ሐዋሪይት እንዴት ባለ መልኩ ነበር ለአገልግሎት የላካቸው? የሰጣቸውን ትዕዛዞች ላይ ተወያይዩባቸው።

<u>ማዛመድ:</u>

7. የተጠራንበትን መጠራት ትልቅነት እያሰብን ምን ያህል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን?
8. ዛሬስ በእኛ እግዚአብሔር ትልቅ ነገርን፣ ዘላለማዊ ሀሳቡን ማከናወን እንደሚችል ታምናለህ? እግዚአብሔር በእኛ ህይወት ተጠቅሞ እንዲሰራ ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?

<u>ማጠቃለያ:</u>

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ሊሆኑ ሁሉን ትተው ሊከተሉት ከነበሩት መሃል 12ቱን ሲለይና ሐዋሪያ ብሎ ሲጠራቸው ተመልክተናል። ጌታ ዛሬም ለአገልግሎት እኛን ከማሰማራቱ በፊት የእርሱ እውነተኛ ደቀ መዛሙርቱ እንድንሆን ይፈልጋል።

<u>የቃል ጥናት - 1ቆሮ 1:27</u>

እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ

# ጥናት 17: የተራራው ስብከት - ክፍል ፩

<u>የምንባብ ክፍል</u> ፡ ሉቃ 6 ፤ 20 - 49

*<u>መግቢያ</u>*፡ ባለፈው ጥናታችንን ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ውስጥ 12ቱን ሲመርጥና ሐዋሪያት ብሎ ሲሰይማቸው ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ጌታ ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ ካስተማራቸው ትምህርቶች ውስጥ አንዱና ትልቁ የሆነውን የተራራው ስብከት ነው የመጀመሪያውን ክፍል እንመለከታለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በቁ.20 ኢየሱስ ማስተማር ሲጀምር ወደ ደቀመዛሙርቱ ዞሮ መናገሩ ምንን ያመለክታል? ከማቴ 5:1 ጋር አስተያይ።
2. ከቁ.20-23 ስንመለከት ድሆችና የምትራቡ ሲል ስጋዊውን ነው ወይስ መንፈሳዊውን፣ ከማቴ 5:3 እና 5:6 ጋር አዛምድ። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ጌታ ብለው ለሚቀበሉት መከራና ለሚከፍሉት ዋጋ የሚጠብቃቸው ብድራት ምንድን ነው? ስለርሱ መከራን ሲቀበሉ (ሲደርስባቸው) ምን ይበላችሁ አለ? ለምን?
3. በቁ.24-26 ስለ ባለጠጎች ኢየሱስ ምን ተናገረ? ለምን?
4. ከቁ.27-31 ለእናንተ ለምትሰሙ ብሎ የሰጠን ትዕዛዝ በዝርዝር ግለፅ። ጠላቶቻችሁን ምን አድርጉ አለ? ክፉ ሊያደርጉባችሁ ለሚወዱስ? የእኛ የሆነውን (መብታችንን) ለሚፈልጉስ?
5. ከቁ.32-34 ባለው ክፍል ውስጥ እንደ ኃጢያአተኞች (እግዚአብሔርን እንደማያውቁ ሰዎች) አታድርጉ የተባሉትን ነገሮች ዘርዝር::
6. ከቁ.35-36 ከኃጢአተኞች በተቃራኒ እንዲህ አድርጉ የተባልነው ምንድን ነው? ለምን? ማንን ለመምሰል ነው የተጠራነው?

<u>ማዛመድ:</u>

7. ከምድራዊና ስጋዊ ስሜት ይልቅ በመንፈስ ድሃ መሆንና መራብን ኢየሱስ ሲያስተምር ጥጋብን (መንፈሳዊ) ይኸውም የእግዚአብሔርን ሙላት በሰማይም ሽልማትን እንዲያመጣ ትረዳህን? ስለዚህ ዛሬ ጥማትህና ረሃብህ ምንድን ነው?
8. እግዚአብሔርን ለመምሰል ከወደድን የእርሱን ባህሪ ማንፀባረቅ፣ የሚጠሉንን በመውደድ መልካምን በማድረግና ያለንን በማካፈል ቸሮችና ርህሩህዎች በመሆን መመላለስ እንደሚገባን አስተዋልክን?

<u>ማጠቃለያ፡</u>

ስለ ጌታ የምንከፍለው ዋጋ ሁሉ ብድራትና ሽልማት አለው። እግዚአብሔር አምላክ የማንም ባለዕዳ አይደለም። "እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።" ራዕ 22፡12 "እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።" ዕብ 6፡10 እግዚአብሔር በሰጠን ዘመን ሁሉ በኑሮአችን እርሱን እየመሰልን የባህሪው ተካፋዮች መሆን ይገባናል።

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 6:38</u>

ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና

## ጥናት 18: የተራራው ስብከት - ክፍል ፪

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 6 ፤ 37 - 49

መግቢያ፡ ባለፈው ሳምንት ጌታ ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ ካስተማራቸው ትምህርቶች ውስጥ አንዱና ትልቁ የሆነውን የተራራው ስብከት ነው የመጀመሪያውን ክፍል ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል እንመለከታለን።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. በቁ. 37-38 ሰው የዘራውን እንዲሁ እንደሚያጭድ ይናገራል:: ስለ መፍረድ፣ ስለ መኮነን፣ ስለ ይቅርታና ስለ መስጠት ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን ተወያዩበት።
2. "ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላልን" ብሎ ኢየሱስ ሊያስተምር የወደደው ነገር ምንድን ነው? በተለይ አገልጋዮች ለሆነው የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድ ነው? አንድ ሰው የሌላውን ድካም ለማውጣት ከመፈለጉ በፊት ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?
3. "በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ በራስህ ዓይን ግን ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም?" በሚለው ሀሳብ መሰረት ግብዞች ሳንሆን ለራሳችን ታማኞች /be honest with ourselves, not hypocrites/ የምንሆነው እንዴት ነው?
4. በቁ. 44-45 መሰረት የሰው መልካምነት ወይም ክፋት በምን ይታወቃል? የዛፍስ መልካምነት በምን ይታወቃል? "በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራል" በሚለው ሃሳብ ላይ ተነጋገሩበት።
5. ጌታ ኢየሱስ በቁ. 46 ላይ "ለምን ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ትሉኛላችሁ" ብሎ ደቀመዛሙርቱ እንዲያደርጉ የፈለገው ምንድ ነው? በዓለት ላይ ቤትን መስራት ማለት ምን ማለት ነው? በአሸዋ ላይስ? ጎርፍ በመጣ ጊዜ በእነዚህ ቦታዎች ላይ የተሰሩት ቤቶች ምን ሆኑ?
6. በወጀብ የማይናውጥና እስከመጨረሻው የሚፀና ህይወት እንዲኖረን የእኛ ኃላፊነት ወይም ድርሻ ምንድን ነው?

ማዛመድ:

7. ሰው ሁሉ የዘራውን (መልካምም ሆነ ክፉ) እንዲያው እንደሚያጭድ ከክፍሉ አስተዋልክን?
8. በአገልግሎት (ሌላውን ለማስተማር) ከመዘጋጀታችን በፊት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?
9. በክርስቶስ አምነን ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ብቻ የፈተና ወጀብ በመጣ ጊዜ እንዳንናወጥ ዋስትና ሊሆነን ይችላልን? በጌታ ቤት እስከ መጨረሻው ፀንተን ለመኖር ምን ማድረግ አለብን?

ማጠቃለያ፡

በዛሬው ጥናት ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መሰረታዊ ነገሮችን ሲያስተምራቸው ተመልክተናል። በመጨረሻም "ስለምን ጌታ ጌታ ሆይ ትሉኛላችሁ የምለውን አታደርጉም" ብሎ ቃሉን ሰምቶ ስለማደረግ የተናገራቸውን መሰረታዊ ሃሳብ አይተናል። እኛም ቃሉን ሰምተን በዘመናችን ሁሉ እንድናደርገው ጌታ በፀጋው ይርዳን።

የቃል ጥናት - ሉቃ 6:41

በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፣ በራስህ ዓይን ግን ያለውን መሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?

# ጥናት 19: ጌታ የተደነቀበት እምነት

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 7 ፤ 1 - 17

መግቢያ: ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ ካስተማራቸው ትምህርቶች ውስጥ አንዱና ትልቁ የሆነውን የተራራው ስብከት ነው የመጀመሪያውን ክፍል ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ጌታ ኢየሱስ በምድር አገልግሎቱ ወቅት የተደነቀበትን እምነት እናያለን።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ከቁ.1-5 ባለው ክፍል ውስጥ መቶ አለቃው ወደ ኢየሱስ የቀረበበትን መንገድ አስረዳ። መቶ አለቃው ኢየሱስን ለምን ፈለገው? ወደ ኢየሱስ የላካቸው ሰዎች እነማን ነበሩ? ለምን?
2. በቁ.6 ላይ ኢየሱስ ጥያቄያቸውን ተቀብሎ ከእርሱ ጋር ወደ መቶ አለቃው ቤት ለምን የሄደ ይመስልሃል?
3. የአይሁድ ሽማግሌዎች ስለ መቶ አለቃው በቁ.3 ላይ የተናገሩትንና መቶ አለቃው ስለራሱ በቁ.6-7 የተናገረው ልዩነቱን አስረዳ? መቶ አለቃው ጥያቄውን ለምን መቀየር አስፈለገው? ስለ መቶ አለቃው ከዚህ ምን ትረዳለህ?
4. በቁ.8 ላይ መቶ አለቃው ስለ ስልጣን አሰራር ምን ተናገረ? ይህንን መናገር ለምን አስፈላገው?ት ከዚህ በመነሳት በጌታ ስልጣን ላይ ያለውን እምነት አስረዳ?
5. ጌታ ኢየሱስ በመቶ አለቃው እምነት ለምን ተደነቀ? ታላቅ እምነትስ ለምን አለው? ከዚህ ስለ እምነት ምን ትረዳለህ?
6. በቁ.11-12 የተገለጠው ታሪክ ምንድን ነው? ለዚህች መበለት ያላት አንድ ልጅ መሞት ምን ያህል ጉዳት እንደነበረው አስረዳ? ኢየሱስ ይችህን መበለት እንዴት ተቀበላት? በምዕራፍ 6:36 ካስተማረው ጋር አነፃፅር። ስለዚህች መበለት ። ጌታ ኢየሱስ ራርቶ ምን አለ? ከዚያስ ምን አደረገ?
7. ህዝቡ ይህንን ተዐምራት በተመለከተ ጊዜ ምላሽ የሰጡበትን ሶስት መንገዶች ግለፅ። ይህ ህዝብ ኢየሱስን በእውነት የተረዳ ይመስልሃል? ለምን? ከተደረገው ተዐምራት የተነሳ ህዝቡ ለምን ፈሩ? ፍርሃትና አምልኮ አብሮ ሊሄድ ይችላል?

ማዛመድ:

8. እውነተኛና የሚታይ እምነት እንዴት ሊገለፅ ይችላል? በጌታ ላይ እንዴት መታመን እንደሚገባን ተረዳህን?
9. ጌታ ኢየሱስ ስለ ሁሉም ሰው (ስለ ባለጠጋው፣ ስለ መበለቲቱ፣ ስለ ታመመው፣ ስለ ሞተውም) ግድ የሚለው የፍቅር አምላክ እንደሆነ አስተዋልክን? ዛሬስ በምታልፍበት በማንኛውም ጉዳይ (ቀላል ወይም ከባድ) ነገር ሁሉ ውስጥ ጌታ ግድ የሚባለው የፍቅር አምላክ እንደሆነ ተረዳህን?
10. የእግዚአብሔር ክብር ባልጠበቅነው መንገድ (ሙታንን በማስነሳት በዚህ ክፍል ውስጥ) ሲገለጥ ፍርሃትን እንደሚያስከትል አየህን? ይህን ፍርሃት ደግሞ እርሱን በይበልጥ ወደማክበርና ወደመውደድ ብሎም ወደማምለክ እንደሚያመጣን ትረዳለህን?

ማጠቃለያ:

ዛሬም ጌታ ኢየሱስ ከምንም በላይ በእርሱ ያለንን እውነተኛ መታመንን ማየት ይወዳል። የልባችን ጥንካሬና የሁኔታዎች መቀያየር በሚያመጣው ጥርጣሬና አለማመን ጌታ ከሚያዝንብን እንደዚህ መቶ አለቃ እውነተኛ እምነት አሳይተን ቢደነቅብን ምነኛ ይሻል ይሆን?

የቃል ጥናት - ሉቃ 7:7

ነገር ግን ቃል ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል።

# ጥናት 20: እምነት ሲፈተን

<u>የምንባብ ክፍል</u> ፡ ሉቃ 7 ፤ 18 - 35

<u>መግቢያ:</u> ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ በምድር አገልግሎቱ ወቅት የተደነቀበትን እምነት ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የእምነት መፈተን እንመለከታለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በቁ.18 ላይ የተጠቀሰው ዮሐንስ ማን ነው? ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ መጥተው ያወሩለት (የነገሩት) ምንድን ነው?
2. የዮሐንስ ምላሽ ምን ነበር? ለምን? ቁ.19
3. በሉቃ 3:1-6 የጌታን መንገድ የጠረገውና ሕዝቡን ለንስሃ በማዘጋጀትና የሕዝቡን ልብ ወደጌታ የመለሰው ዮሐንስ ዛሬ ስለምን ተጠራጠረ?
4. የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ኢየሱስ መጥተው መልዕክቱን ሲያቀርቡ የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበረ? ቁ.20-23 ኢየሱስ ለምን "አዎን እኔ ነኝ" ማለት ሲችል ለምን እንዲህ መለሰ? የኢየሱስ መልስ ለዮሐንስ በምን መልኩ ሊረዳው ይችላል ትላለህ?
5. በቁ.23 ላይ "በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው? ለምን? ተወያዩበት።
6. የዮሐንስ መልዕክተኞች ከሄዱ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡን ስለዮሐንስ ምን አለ? በቁ .28 " . . .በእግዚአብሔር መንግስት ከሁሉም የሚያንሰው ይበልጠዋል።" ሲል ኢየሱስ ስለ ዮሐንስ ያለውን እንዴት ትረዳለህ? ምን ማለቱ ነው? ተወይዩበት።
7. ጌታ ኢየሱስ "የዚችን ትውልድ ሰዎች በምን አስመስላቸዋለሁ? ማንንስ ይመስላሉ?" ብሎ የመሰለው በምንድ ነው? ለምን በዚህ ሁኔታ ትውልዱን የመሰለው ይመስልሃል?

<u>ማዛመድ:</u>

8. በአንድ ወቅት ለተጠራንበት ጥሪ ብዙ ተግተን ሰርተን ድንገት ያ ሁሉ መታመንና ጥንካሬ ከእኛ መሸሽ ሲጀምር ወይንም ሁኔታዎች ሲቀያየሩ ምን ማድረግ አለብን? ዮሐንስ ወደ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን መላኩ የጌታን መሲህነት መጠራጠሩ እንደሆነ ትረዳለህን?
9. "ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ" ጌታ እንዳለ ዛሬ ምን አይተህ (ምን ተስፋ አድርገህ) ነው ጌታን የምትከተለው? የምታገለግለው? ቆም ብለን ራሳችንን እንመርምር።

<u>ማጠቃለያ:</u>

ዛሬ እኛም በፈተና ውስጥ ፀንተን በመቆም ጌታን መፈለግ መውጫን ጌታ እያዘጋጀ ከእምነት ወደ እምነት እንድንሻገር ይረዳናል። "ማንም የቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ" እንደሚል ቃሉ ሁልጊዜ ህይወታችንን በጌታ ፊት እየመረመርን በጌታ ፀጋ ልንመላለስ ይገባናል።

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 7:35</u>

ጥበብም ለልጆችዋ ሁሉ ጸደቀች።

# ጥናት 21፡ የኃጢአት ስርዐየትና የንስሃ ደስታ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 7 ፤ 36 - 50

*መግቢያ፡* ባለፈው ጥናታችን ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የእምነት መፈተን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ብዙ ኃጢአትዋ የተሰረየላትን ሴት ያደረገችውን ነገር እንመለከታለን።

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. በቁ 36-37 ላይ ኢየሱስ የት ነበረ? በግብዣው ላይ ሳትታደም የተገኘችው እንግዳ ማን ናት? ለምን በዚህ ስፍራ ተገኘች? በክፍሉ ስለእርሷ ማንነት የተፃፈና የምናውቀው ምን ነገር አለ?
2. በቁ 38 ላይ ይች ሴት ምን አደረገች ይላል? በአይሁድ ባህል እንዲህ አይነት ሴቶች ብዙ ህዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ መገኘት ባይፈቀድላቸውም ይህችህ ሴት ወስና ይህን እርምጃ መውሰዷ ምን ያሳያል?
3. ፈሪሳዊው የሆነው ሰው አይቶ በልቡ ምን አሰበ? እርሱ በጠራው ግብዣ ላይ ያልጠበቀው በመሆኑ የተሰማው ስሜት ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ? ያፈረ ይመስልሃልን?
4. ኢየሱስ ፈሪሳዊው ያስብ የነበረውን የልቡን አውቆ ምን አለው? የልቡን ሃሳብ ማወቁ "ይህ ነብይ ቢሆን . . . " ብሎ ላሰበው ፈሪሳዊ በእርግጥም ኢየሱስ ነብይ እንደነበረ አንዱ ማረጋገጫ እንደሆነ ትመለከታለህን?
5. በቁ. 41-42 ኢየሱስ የተናገረው ምሳሌ ምንድን ነው? ስምዖንን ሊያስተምረው የፈለገው ነገር ምንድን ነው? ከሉቃ 6: 41 ጋር በማዛመድ ተወያዩ።
6. በክፍሉ ፈሪሳዊውና ኃጥያአተኛዋ ሴት ኢየሱስን በራሳቸው መንገድ ሲያስተናግዱት እናያለን። ብዙ ይቅር የተባለውና ብዙ ያደረገው (የወደደው) ማን ነው? ጥቂት ያደረገውስ? ከዚህ ምን ትማራለህ? ፈሪሳዊውና ሐጥአተኛዋን ሴት በማነፃፀር ተወያዩ።

*ማዛመድ:*

7. ጌታ ብዙ ምህረት አድርጎልናል እንዲሁም ህይወታችንን ከሞት እንዳዳነ አውቅን በምን ዓይነት መንገድ ምላሽ እየሰጠን እንገኛለን?
8. ፈሪሳዊው ለራሱ ክብር ሲጠነቀቅ ነገር ግን ኃጢአተኛዋ ሴት ክብሯን በሙሉ ጥላ በኢየሱስ ፊት ስትሆን ተመልክተናል። ምን ያህል ዛሬ በዙሪያችን ያለው ሳይጨንቀን ራሳችንን በጌታ ፊት እናዋርዳለን?

*ማጠቃለያ፡*

በዛሬው ጥናታችን ጌታ ኢየሱስ ከፈሪሳዊው መስተንግዶና ግብዣ ይልቅ በኃጢአተኛዋ ሴት ሲደነቅ ተመልክተናል። እግዚአብሔር አምላክ ሁሌም ከብዙ መስዋዕት ይልቅ መታዘዝን፣ ለታይታ ከሚደረግ ብዙ ድግስ ይልቅ ከልብ በሆነው አምልኮና ትህትና ይደሰታል።

## የቃል ጥናት - ሉቃ 7:50

ሴቲቱንም፡- እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ አላት።

## ጥናት 22: የዘሪው ምሳሌ

<u>የምንባብ ክፍል</u> **: ሉቃ 8 ፤ 1 - 21**

*<u>መግቢያ:</u>* ባለፈው ጥናት ብዙ ኃጢአትዋ የተሰረየላትን ሴት ያደረገችውን ነገር ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ኢየሱስ የተናገረውን የዘሪውን ምሳሌ እንመለከታለን።

*<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>*

1. ኢየሱስ በገሊላ ከተማና መንደሮች እያለፈ የሚያስተምራቸው ትምህርት (ስብከት) መልዕክቱ ምን ነበር?
2. ለኢየሱስ አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጡት እነማን ነበሩ? በገንዘባቸው ሊያገለግሉት የወሰኑት ከምን የተነሳ ነበር?
3. በቁ. 4-8 ኢየሱስ በምሳሌ ያስተማረው ትምህርት ላይ ዘሩ የተዘራባቸው ቦታዎች የት የት ነበሩ? ፍሬያማነታቸውስ እንዴት ነበር?
4. ቁ. 9-11 ኢየሱስ ምሳሌውን ተናግሮ በጨረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርት ቀርበው "ይህ ምሳሌ ምንድ ነው?" ብለው ሲጠይቁት እንመለከታለን። ይህን ጥያቄ ለምን ጠየቁ? የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበር? ከኢሳ 6:10 እና ከመዝ 78:2 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
5. በቁ. 15 ላይ "በበጎ ልብ ቃሉን ሰምተው የሚጠብቁት" ይላል። በበጎ ልብ ቃሉን መስማት እንዴት ነው። ተወያዩበት።
6. በቁ. 12-15 መሰረት ዘሩ ምንድን ነው? ዘሪውስ ማን ነው? ዘሩ የተዘራበት ቦታ ምንን ይወክላል? አራቱ የመስማት አይነቶች ምን ምን ናቸው? ውጤታቸውስ? ዘሪው ለምን መልካምን መሬት እየመረጠ አልዘራም?
7. በቁ. 16-18 ባለው ክፍል ላይ ኢየሱስ ከላይ ከተናገረው ምሳሌ ጋር ምን ተያያዥነት ያለው ይመስልሃል?
8. በቁ.19-20 ላይ ኢየሱስ እናቱና ወንድሞቹ እንደሚፈልጉት መልዕክት ሲነገረው የመለሰላቸው መልስ ምን ነበረ? ምላሹ ለስጋ ዘመዶቹ ዕውቅና/ከበሬታ እንዳልሰጣቸው የሚያመለክት ነውን? ካልሆነ ምን ለማለት የፈለገ ይመስላችኋል?

*<u>ማዛመድ:</u>*

9. የልብ መዘጋጀት ከሰው መሆኑን ተገንዝበህ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት በቀረብክ ጊዜ እንዴት ባለሁኔታ መዘጋጀት እንደሚገባን ትረዳለህ?
10. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

*<u>ማጠቃለያ:</u>*

የእግዚአብሔር ቃል በተዘጋጀ ልብ መስማት፣ የሰሙትንም መረዳትና በእምነት መታዘዝ ፍሬያማ ያደርጋል። ነገር ግን "የልብ መዘጋጀት ከሰው ነው፤ የምላስ መልስ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።" እንደሚል ቃሉ እኛ ልባችንን በማዘጋጀት የራሳችንን ድርሻ ብንወጣና ለሰማነው ቃል ብንጠነቀቅ እግዚአብሔር አምላክ በብዙ ፍሬ ይባርከናል።

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 8:8</u>

በመልካም መሬት ላይ ወደቀ በበቀለም ጊዜ መቶ እጥፍ አፈራ።

# ጥናት 23: ኢየሱስን ብዙ ተአምራትን አደረገ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ **8 ፤ 22 - 56**

*መግቢያ:* ባለፈው ጥናታችን ጌታ ኢየሱስ የዘሪውን ምሳሌ በመጥቀስ እምነት ቃሉን ከመስማት እንደሆነ ያስተማራቸውን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ይኸው እምነት የሚያድገው በፈተና ውስጥ መሆኑን ሊያሳያቸው ደቀ መዛሙርቱን በወጀብ መሀል ዝም ሲላቸው እንመለከታለን።ል

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. በቁ.20-23 ባለው ታሪክ መሰረት በታንኳ ላይ ሆነው ሳሉ በደረሰባቸው ወጀብ የተነሳ በደቀ መዛሙርቱ ላይ የፈጠረባቸው ስሜት ምን ይመስል ነበረ? የኢየሱስ ምላሽስ?
2. ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን ተዓምራት ሲያዩ ይህ የመጀመሪያው እንዳልሆነ እስካሁን ባነበብናቸው ምዕራፎች አይተናል። ሆኖም ይሄኛው ተዐምር በመካከላቸው ትልቅ ጥያቄ ሲፈጥር እንመለከታለን። ጥያቄው ምን ነበረ? ለምንስ ተፈጠረባቸው?
3. በቁ.26-36 ላይ በአጋንንት የታሰረው ሰው የነበረበት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ኢየሱስንስ ባየ ጊዜ ምን ተፈጠረ? ኢየሱስ በአጋንንት የታሰረውን ሰው ነፃ ካወጣ በኋላ ፈውሱ ነፃ በወጣው ሰውዬና በአከባቢው የፈጠረውን ለውጥ ተወያዩበት።
4. ከቁ.40-56 ኢየሱስ የሙክራብ አለቃውን ልመና ሰምቶ ወደቤቱ ሲሄድ በመንገድ ላይ ምን አጋጠመው? በክፍሉ የተጠቀሰችው ሴት የጤና፣ የኑሮና የኢኮኖሚ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?
5. ሴቲቱ መፈወስዋን ያወቀችው መቼ ነበር? ብዙዎች በሚያጨናንቁበት ጊዜና ወቅት ለእርሷ ግን እንድትፈወስ ምክንያት የሆናት ምንድን ነው? ኢየሱስ "አንድ ሰው ዳሰኛል ኃይል ከእኔ እንደወጣ አውቃለሁ" ብሎ ሲናገር ሴቲቱ ፈውሷን ከመመስከር ይልቅ መሰወርን ለምን የመረጠች ይመስልሃል? ኢየሱስ በሕዝብ ፊት እንድትመሰክር ማድረጉ ጠቀሜታው ምንድን ነው? የምስክርነትን አስፈላጊነት ተወያዩበት።
6. ኢየሱስና ኢያኢሮስ ገና በመንገድ ላይ ሳሉ የልጅ መሞት መርዶ ሲነገረው ኢያኢሮስ ምን የተሰማው ይመስልሃል? ኢየሱስ ምን አለው? በእግዚአብሔር የማዳን ስራ ውስጥ የእኛ ድርሻ ምን እንደሚሆን ተረዳህ?
7. ኢየሱስ ወደ ኢያኢሮስ ቤት ሲደርስ የሞተችዋን ልጅ አይቶ ምን አለ? ከዚህ ስለ እግዚአብሔር አስራር ምን ትማራለህ? ለሰው የዘገየ በሚመስል ወቅትና ጊዜ ላይ፣ ምናልባትም አለቀ ተቆረጠ በተባለው ነገር ላይ ህይወትን መቀጠል እንዲቻለው ትረዳለህን?

*ማዛመድ:*

8. በክፍሉ ጌታ ኢየሱስ ስለ እምነት በተደጋጋሚ ሲናገር ተመልክተናል። "እምነታችሁ የት ነው?" (ቁ.25)፣ "ልጄ ሆይ እምነሽ አድኖሻል" (ቁ.38)፣ "እመን ብቻ ትድንማለች" (ቁ.50)። ጌታ ዛሬ በህይወትህ እምነትን ፈልጎ ያጣበት ነገር ይኖር ይሆን? የእምነትን አስፈላጊነት ተወያዩበት።
9. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

*ማጠቃለያ:*

አምላካችን እግዚአብሔር በተፈጥሮ፣ በበሽታ፣ በአጋንንትና በሞት ላይ እንኳን ሳይቀር ስልጣን እንዳለው ተመልክተናል። ለአንዳንዶች የዘገየ ቢመስላቸውም ጌታ በእርግጥ ተስፋውን ሊፈፅም ከቶ አይዘገይም። ከእኛ የሚጠበቀው እግዚአብሔርን ማመንና እርሱን በትዕግስት መጠበቅ እንደሆን ከክፍሉ እንማራለን።

*የቃል ጥናት - ሉቃ 8:48* ልጄ ሆይ፤ እምነትሽ አድኖሻልና በሰላም ሂጂ

## ጥናት 24: አምስት እንጀራና ሁለት ዓሳ

*የምንባብ ክፍል* : ሉቃ 9 ፤ 12 - 17

*መግቢያ:* ባለፈው ጥናት ኢየሱስ እምነት የሚያድገው በፈተና ውስጥ መሆኑን ሊያሳያቸው ደቀ መዛሙርቱን በወጀብ መሀል ዝም ሲላቸው ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ኢየሱስ አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሳ ባርኮ አምስት ሺህ ሰዎችን እንደመገበ እንመለከታለን።

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. በቁ. 12-13 መሰረት የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ምን ነበር? ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰላቸው? በስፍራው የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛት ምን ያህል ነበር?
2. ቦታው ምድረ በዳ፣ ጊዜው ምሽት፣ በእጅ ያለው ምግብ ለተሰበሰቡት በማይበቃበት ሁኔታ ጌታ ኢየሱስ "እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው" ብሎ ማለቱ ለደቀ መዛሙርቱ ምን ያህል የሚከብድ ይመስልሃል? ኢየሱስ በዚህ ሊያስተምራቸው የወደደው ነገር ምንድን ነው? ከዮሐ 6:6 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
3. ኢየሱስ በክፍሉ ለደቀ መዛሙርቱ የማይቻለውን ጥቂቱን የማባዛት ተአምር ከማድረጉ በፊት እነርሱ ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገሮች ሲጠይቃቸው እንመለከታለን። ኢየሱስ ተዐምርን እንዲያደርግ ደቀ መዛሙርቱ ምን ምን ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር?
4. ኢየሱስ አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሳ ይዞ ከባረከ በኋላ ስለ ተፈጠረው ተአምር ተወያዩበት። በደቀ መዛሙርቱና በሕዝቡ ውስጥ ሊፈጠር የሚችለውን ስሜት በራስህ አገላለጽ አስረዳ።
5. ኢየሱስ የበረከቱ ምንጭ (source) ደቀ መዛሙርቱም የበረከቱ አከፋፋይ (distributor) በመሆን ተአምራቱ እንደተከናወነ እናያለን። በመጨረሻ በቁ. 17 መሰረት ምን ሆነ? ዮሐ 6:14 በማንበብ ተወያዩበት።

*ማዛመድ*:

6. በአስቸጋሪ ስፍራና ጊዜ በእጃችን ያለው ነገር ጥቂትና የማይበቃ በሆነበት ወቅት ምን ማድረግ እንደሚገባ ከዛሬው ጥናት የተማርከውን አካፍል። ከዚህ በፊት እግዚአብሔር በህይወትህ በእንዲህ ባለ ሁኔታ ያደረገው ተአምር ይኖር ይሆን? ምስክርነት ካለህ ለህብረቱ አካፍል።
7. እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ፈፅሞ የማይቻለውን ተአምር በህይወታችን ከማድረጉ በፊት አንዳንዴ ለእኛ የሚቻለውን ትንሹን ነገር እንድናደርግ ይፈልጋል። ምሳሌ በመስጠት ተወያዩበት።
8. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

*ማጠቃለያ፡*

ኢየሱስ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሳ አምስት ሺህ ሰዎችን በአስደናቂ ተአምር እንደመገበና ሁሉም ጠግበው በረከቱ እንደተረፈ በዛሬው ጥናት ተመልክተናል። እውነት ነው፣ የሰዎች ዕለት እንጀራም ጉዳይ ኢየሱስን ይገዳዋል። ይሁን እንጂ የክርስቶስ ኢየሱስ የዚህ ተአምር አላማ ግን የተራቡ ሰዎችን ከመመገብ ያለፈና የኢየሱስን መሲህነት እንዲሁም ለሰዎች ድህንነት የእግዚአብሔርን ሰጪነት (God's gracious provision) በግልፅ የሚያሳይ ነው።

### የቃል ጥናት - ሉቃ 9:17

*ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ ከእነርሱም የተረፈውን ቁርስራሽ አስራ ሁለት መሶብ ወሰዱ።*

## ጥናት 25: እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?

የምንባብ ክፍል : ሉቃ 9 ፤ 18 - 22

*መግቢያ*፡ ባለፈው ጥናት ኢየሱስ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሳ የባረከበትን ተአምር ተምልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን ስለእርሱ ያላቸውን የግል የእምነት ምስክርነት (Personal confession of faith) ሲጠይቃቸው እንመለከትናል።

*የመወያያ ጥያቄዎች:*

1. ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን የእምነታቸውን መግለጫ (ስለ ኢየሱስ ያላቸውን የግል ምስክርነት) ከመጠየቁ በፊት ምን አደረገ? ከዚህ ስለ ኢየሱስ ልምምድ ምን እንማራለን።
2. በቁ. 18 እና 19 ላይ ያለው ጥያቄና መልስ ምን ነበር?
3. ኢየሱስን ማወቅ ለአንድ አማኝ ያለውን ጠቀሜታ ተወያዩበት።
4. "እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ" ብሎ ለጠየቃቸው ጥያቄ ደቀ መዛሙርቱን በመወከል ብዙውን ጊዜ የሚናገረው ጴጥሮስ ምን ብሎ መለሰ? እንዴትስ ሊመልስ ቻለ? ከመለሰው መልስ በመነሳት ጴጥሮስ የጌታ ኢየሱስን ፍጽም አምላክነት የተረዳ ይመስልሃልን?
5. በሌላ ክፍል በማቴ 16:17 ላይ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ስጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁህ ነህ" ይላል። ጌታን በሚገባ ለማወቅ የመገለጥን አስፈላጊነት ተወያዩበት።
6. በተያያዘ ክፍል (ማቴ 16፡ 18) ላይ "በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ" ባለው ሃሳብ ላይ ተወያዩበት።
7. በቁ. 21-22 ላይ ኢየሱስ ምን ብሎ ነገራቸው? ለማንም እንዳይናገሩ አስጠንቅቆ ያዘዛቸው ለምን ይመስልሃል? በሉቃ 24:44-48 መሰረት አሁን ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን ደቀ መዛሙርቱ በትክክል የተረዱት ይመስልሃልን?

*ማዛመድ*:

8. እናንተስ ኢየሱስን ማን እንደሆነ ትላላችሁ? በህይወታችሁ ከተለማመዳችሁት በመነሳት ኢየሱስ ለእናንተ ማን እንደሆነ ለህብረቱ ተናገሩ። (የቡድኑ አስጠኚ ፡ እባክዎ ሁሉም በዚህ ሃሳብ እንዲናገሩ እድል ይስጡ)።
9. የኢየሱስን ማንነት በሚገባ ማወቃችን ለመንፈሳዊ ህይወት ጉዞአችን እንዲሁም ለአገልግሎታችን ያለውን ጠቀሜታ አስረዳ።
10. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

*ማጠቃለያ፡*

ኢየሱስ "እናንተስ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ?" ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ጴጥሮስ "አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" በማለት የመለሰውን መልስ ተመልክተናል። ዛሬም ለእኛ የኢየሱስን ማንነት አጥርተን ማወቃችንና ማመናችን ዘላለማችንን የሚወስን ትልቅ ነገር ነው። ስለ ኢየሱስ የተሳሳተ ግንዛቤ ይዞ እግዚአብሔር ጋር መድረስ አይቻልምና። ዮሐ 8:24 , 1ዮሐ 4:1-3

*የቃል ጥናት - ማቴ 16:16*

አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ

# ጥናት 26: የመገለጥ ተራራ

የምንባብ ክፍል ፡ ሉቃ 9 ፤ 28 - 36

መግቢያ፡ ባለፈው ጥናታችን ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት "አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" በማለት ተገለጦለት የተናገረውን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ላይ በደቀ መዛሙርቱ ፊት እንደተለወጠ /transfiguration/ እንዲሁም እግዚአበሔር አብ ከሰማይ የመሰከረውን እንመለከታለን።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1. በቁ 29 ኢየሱስ ከጴጥሮስ ከዮሐንስና ከያዕቆብ ጋር ወዴት ሄደ? ለምን ሄደ? በዚያ ስፍራ ምን ሆነ?
2. በቁ.29 ላይ "የፊቱ መልክ ተለወጠ" /transfiguration/ ይላል። ይህን አስደናቂ ክስተት እንዴት ትገልፀዋለህ?
3. በቁ. 30 ላይ በዚህ የመገለጥ ተራራ ላይ የተገኙ አዳዲስ እንግዶች እነማን ናቸው? ከኢየሱስ ጋር ስለምን ይነጋገሩ ነበር? እንዚህ የተገለጡ ሰዎች በብሉይ ዘመን ምንን ይወክላሉ? የተገለጠውን ክብርና የተገኙትን ሰዎች ስትመለከት ይህ ጊዜ ምን ያህል ልዩና አስደናቂ ነው ትላለህ?
4. እነዚህ ታላላቅ ሰዎች ስብሰባ በሚያደርጉበት በዚህ አስደናቂ ወቅት ጴጥሮስ ዮሐንስና ያዕቆብ ምን ያደርጉ ነበር?
5. ከእንቅልፍ ሲነቁ ጴጥሮስ ኢየሱስን ምን ብሎ ጠየቀው?
6. በዚያ ተራራ ላይ ለመኖር ጴጥሮስ ያቀረበው ጥያቄ ኢየሱስ በምድር ሊያደርገው ካለው ዓላማ ጋር እንዴት ታስተያየዋለህ?
7. በቁ. 34-36 ላይ ምን ሆነ?
8. በመጽሐፍ ቅዱስ የሙሴ ስም በተነሳ ጊዜ ሁሉ ስለ ህግ አብሮ ይነሳል። ስለዚህም ሙሴ የህግ አባት ነው። ኤልያስ ደግሞ የነብያት ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ሙሴንና ኤልያስን በደመና ጋርዶ ኢየሱስን ግን "የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" ማለቱ ምን ያሳያል? "እርሱን ስሙት" በሚለው ሃሳብ ላይ ተወያዩበት።

ማዛመድ:

9. እግዚአብሔር አምላክ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን፣ በቅዱሳኑ መሃከል ክብሩን ሲገልጥ ያዕቆብም እንዳለ "በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔም አላወቅሁም ነበር" (ዘፍ 28:16) እንዳለ እኛም መንፈሳዊ እንቅልፍ ተጫጭኖን የእግዚአብሔር ክብር ምን ያህል እንዳመለጠን ታስተውላለህን? የእግዚአብሔርን እውነተኛውን ክብር ሳናይ ከእንቅልፍ ተነስተን የምንሰጠው አስተያየት የተዛባና ከፈቃዱ የሚቃረን መሆኑንስ ትገነዘባለህን?
10. ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በህግ በነብያት ተናግሮ አሁን ሁሉን ወራሽ ባደረገው በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ እንደተናገረን አውቀህ ይህ ላልገባቸውና እስካሁን በህግና በትንቢት ቃል መዳንን ለሚሹ ምን ያህል የምስራች ወንጌሉን ትናገራለህ?
11. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

ማጠቃለያ፡

ኢየሱስ ለእኛ የእግዚአብሔር የክብሩ ነፀብራቅና የባህሪው ምሳሌ ሆኖ ተገልጦልናል። እግዚአብሔር አምላክ የወደደው እርሱንም ስሙት ያለው ሙሴን (ህግን) ወይንም ኤልያስን (ነብያትን) ሳይሆን ልጁን ኢየሱስ መሆኑን አውቀን ይህን የተገለጥልንን እውነት ለሌሎች ልናካፍል ይገባናል።

የቃል ጥናት - ሉቃ 9:35

የመረጥሁት ልጄ ይሄ ነው፤ እርሱን ስሙት

# ጥናት 27: ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?

<u>የምንባብ ክፍል</u> ፡ ሉቃ 9 ፤ 46 - 50, 14 ፤ 7 - 11

<u>መግቢያ</u>: ባለፈው ጥናታችን ኢየሱስ በተራራ ላይ ከሙሴና ከኤልያስ ጋር ሲነጋገር ሳለ እግዚአብሔር አምላክ ሙሴንና ኤልያስን በደመና ጋርዶ ኢየሱስን ግን "የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" ያለውን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን በደቀ መዛሙርቱ መካከል ለተነሳው ክርክር ጌታ ኢየሱስ የሰጠውን መልስ እናያለን።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች:</u>

1. በቁ 46 ላይ የተነሳው ክርክር ምን ነበር?
2. ኢየሱስ የልባቸውን ሀሳብ አውቆ ምን አደረገ? ምንስ አላቸው?
3. በቁ. 49 -50 ላይ የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ምን ነበረ? ኢየሱስስ ምን ብሎ መለሰላቸው? በዚህ ስፍራ ደቀ መዛሙርቱ ከእነርሱ ጋር ስላልሆኑ ግለሰቦችም ሆነ ግሩፖች ያላቸው አመለካከት ምን ይመስል ነበር። ኢየሱስ ሊኖራቸው ስለሚገባ አመለካከት የተናገረውን ተወያዩበት።
4. በም 14:7-11 ላይ ኢየሱስ ምሳሌን ሊነግራቸው የጀመረው ምን አይቶ ነበር? ምሳሌው ምን ነበር?
5. ጌታ ኢየሱስ እንዳስተማራቸው የእውነተኛ ከፍታ ሚስጥሩ ( መንገዱ) ምንድን ነው?
6. ትዕቢት ምንድን ነው? ትህትናስ? እንዴት በሰው ልብ ውስጥ ሊፈጠሩ ይችላሉ? ምሳ 18፡12 ምሳ 11፡2 ሮሜ12፡16
7. የዓለም የከፍታው መንገድና የእግዚአብሔር የከፍታው መንገድ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ? እግዚአብሔር ሰዎችን ከፍ የሚያደርግበት ሚዛኑ (መንገዱ) ምንድን ነው?

<u>ማዛመድ</u>:

8. በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ራሱ ዝቅ አድርጎ ደቀ መዛሙርቱን ትህትናን ያስተማራቸው መቼ ነበር? ጌታ ኢየሱስ ምን አደረገ? ዮሐ 13:4-15 አንብቡ።
9. ዛሬ እኛም በቤታችን፣ በቤተክርስቲያን፣ በቅዱሳን መካከል ራሳችንን እንዴት ዝቅ ማድረግ አለብን?
10. በሕይወትህ ራስህን ዝቅ በማድረግህ እግዚአብሔር ከፍ ያደረገህ፣ ወይንም ራስህን ከፍ ስታደርግ የተዋረድክበት የህይወት ምስክርነት ካለህ ለሌሎች አካፈል።
11. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ/ሽ? ለቡድኑ አካፍል/ይ።

<u>ማጠቃለያ፡</u>

እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ፈፅሞ ይቃወማል፤ ለትሁታን ግን ፀጋን ይሰጣል። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ለዚህ ትልቅ ምሳሌያችን ነው። እርሱ ጌታና አምላክ ሆኖ ሳለ ዝቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቧል። ኢየሱስ ራሱ በማቴ 11:29 ሲናገር "እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና" ብሎ ተናግሯል። ዛሬ እኛም "አንተ/አንቺ ትብስ" በመባባል በትህትና ህይወት ብንመላለስ እግዚአብሔር ደስ ከመደሰኘቱም ባሻገር በሰው ሁሉ ፊት ከፍ ያደርገናል። የትዕቢትን ነገር አታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ። ሮሜ 12፡16

<u>የቃል ጥናት - ሉቃ 14:11</u>

ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፤ ራሱንም የሚያዋርድ ከፍ ይላል።


PHOENICIA
MEDITERRANEAN SEA
GALILEE
Bethsaida Julias
BASHAN
Capernaum
Tabigha
Gergesa
Cana
Magdala
MT. CARMEL
KISHON R.
SEA OF GALILEE
Tiberias
Hippos
Sepphoris
Nazareth
YARMUK R.
DECAPOLIS
Nain
JORDAN R.
The Beginning of Christ's Ministry
SAMARIA
FROM EGYPT
Scythopolis
(Beth-shan)
Bethabara
TO AND FROM THE WILDERNESS OF JUDAH
En-Ganniin
(Ginaea)
TO AND FROM JERUSALEM
Bible History Online